# አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት ለኢትዮጵያ



# የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው!!!

ከህዳሴ ኢትዮጵያ

ሓምሌ 30፣ 2008 ዓ.ም.

hidaseethiopia@yahoo.com

## Table of Contents

1 መግቢያ .... 3
2 አሁን በዓለማችን ያለ የኢኮኖሚ ስርዓት አማራጭ .... 6
2.1 ሊበራሊዝም .... 8
2.2 ልማታዊ መንግስት .... 10
2.3 መሰረታዊ ልዩነቱ ምንድን ነው? .... 10
2.4 ከልማቱ የዜጋ/ህዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ .... 11
2.5 በዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጥያቄ ያለው አንድነትና ልዩነት .... 12
2.5.1 ሊበራል ዴሞክራሲ .... 13
2.5.2 አብዮታዊ ዴሞክራሲ / ልማታዊ ዴሞክራሲ .... 13
3 እነዚህ አማራጭ ርዕዮቶች በኢትዮጵያ ያላቸው ማሕበራዊ መሰረት ምን ይመስላል? .... 15
4 በአማራጮቹ በመንግስታዊ አወቃቀር ያለው አንድነትና ልዩነት .... 18
4.1 የሊበራል ዴሞክራሲ ተከታዮች .... 19
4.2 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተከታዮች .... 19
5 አሁን በአገራችን እየታየ ያለው ችግር ምንድን ነው? .... 20
5.1 ኪራይ ሰብሳቢነት የስርዓታችን ዓደጋ .... 22
6 የኪራይ ሰብሳቢነት መደበቂያ ዋሻዎች .... 25
6.1 ትምክህተኝነት .... 25
6.2 ጠባብነት .... 29
6.3 የትምክህትና ጠባብነት አንድነት .... 30
7 የተረጋጋች የለማች ኢትዮጵያ የመፍጠር ጉዳይ ለመንግስት ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም 32
8 ማጠቃለያ .... 35

# 1 መግቢያ

ኢትዮጵያ አገራችን ከአለማችን ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀልጣፋ እድገት ከሚያረጋግጡ አገራት አንድዋ ለመሆን በቅታለች፣ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊት አገር ለመገንባት የተደረገው ጥረት አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው የተደረጉት 5 ወቅታቸውን የጠበቁ አገራዊ ምርጫ ከጊዜ ወደጊዜ እድገት እየታየባቸው የተፈፀሙ፣ ፍፁም ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና በህዝብ ዘንድ ተአማኒነት እያገኙ የመጡ መሆናቸው አንዱ አስረጅ ነው፡፡ በዲፕሎማሲውም በኩል አገራችን ከጊዜ ወደጊዜ ተሰሚነቷ እያደገ በመምጣት በትላልቅ የዓለማችን መድረኮች አፍሪካን ወክላ እንድትገኝ፣ በዓለማችን ሰላምና መረጋጋት በማስፈን ተግባር ከአለማችን ቀዳሚ ከሚባሉ አገራት ጎን መሰለፍ እንደቻለች በተጨባጭ አሁን የምናየው ጉዳይ ነው፡፡

የስርዓታችን ዋነኛው አደጋ ተብሎ የተለየው ኪራይ ሰብሳቢነት ከምንጩ ለማድረቅ በተደረገው እንቅስቃሴ አበረታች ውጤቶችን በማስመዝገብ ላይ ትገኛለች፡፡ በገጠር የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነቱን በመናድ በምትኩ በልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለመተካት የተደረገው ጥረት ከፍተኛ ደረጃላይ የደረሰ ሲሆን፣ በከተማ ከፍተኛ ጥረት ቢደረግም፣ ኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ ገና የበላይነቱ እንደያዘና በቀጣይ የተጠናከረ ትግል እንደሚያስፈልገው በግልፅ ኣሳይቶናል፡፡

ይሁንና ከነዚህ ትላልቅ ስኬቶችና ውጤቶች በተቃራኒ ህዝብ የሚያማርርባቸው ችግሮች መኖራቸው የማይካድ ጉዳይ ሆኖዋል፡፡ የነዚህ ችግሮች መገለጫም የመልካም አስተዳደር እጦትና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮች ናቸው፡፡ ***ይህ የሚያሳየው ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ልማቱ በማረጋገጥ ሂደትና ያስመዘገብነው ውጤትን የሚመጥን መልካም አስተዳደር አለማስፈንና ኪራይ ሰብሳቢነት በመዋጋት በተለይ በከተማው የተደረገው እንቅስቃሴ ህዝቡን ከሚጠብቀው ደረጃ የወረደ በመሆኑ እዚህም እዛም የተለያዩ ቅሬታዎች ሲነሱ ይታያሉ፡፡*** ይህን በሚገባ በመገምገምና ችግሮችን በመረዳት መንግስት ከህዝቡ ጋር ሆኖ ለመፍታት በሚፍጨረጨርበት ጊዜ፣ ትምክህተኞችና ጠባቦች በመንግስትና ህዝብ መሃከል ሰፊ ክፍተት ተፈጥሯል በሚል የተሳሳተ ግምገማ ዕድሉን አገኘነው ወይም ኣጣነው ዛሬ ነው በማለት ያለ የሌለ አቅማቸው በመጠቀም በፀረ-ህዝብና ሕገወጥ ተግባር በግላጭ መንቀሳቀስ ጀምሯል፡፡

ኢህአዴግ በመራው የትጥቅ ትግል በከፍተኛ አመራርነት ተመድበው ሲመሩና ትግሉን ለድል ያበቁ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር የነበሩ ግን ደግሞ ኢህአዴግ የመበስበስና የመዝቀጥ አደጋ

ደርሶበት በነበረበት ጊዜ ከዝቅጠትና ከመበስበስ ወጥተው ***መድረኩን የሚፈልገው ቁመና ሊይዙ ባለመቻላቸው የተሃድሶው ማዕበል የተፋቸው ግለሰቦች ሳይቀር ዕድሉ አገኘነው አጣነው ዛሬ ነው በሚል ፈሊጥ ከትምክህተኞችና ጠባቦች ጎራ ተሰልፈው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን ጥላሸት ሲቀቡት ይታያሉ፡፡*** እነዚህ ግለሰቦች ተሃድሶው ከተፋቸው ከ15 ዓመት ቦኋላ በውስጣቸው ታፍኖ የነበረውን ቂምና ጥላቻ አሁን አፍ አውጥተው ሲዘከዝኩት ይሰማል፡፡

የቀድሞ የኢህአዴግ ሊቀመንበር ***ክቡር መሪያችን ኣቶ መለስ ዜናዊ*** በአንድ ወቅት ስለ የተሃድሶው ጉዞና የአንጃው እንቅስቃሴ ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ትግል አንፃር ሲገልፁ ትዝ ያለኝ አንድ ነገር ነበር፣ እሱም ***ህዝባዊ ወገንተኝነት ያለው ወገን የመታገያው መስመር አንድና አንድ ብቻ ነው፣ እሱም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ብቻ ነው ከዚህ ውጭ ያለው ሁሉ የጥገኛና የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ነው*** ኣሉና እነዚ አፈንጋጭ አንጃም በድርጅታችን ውስጥ እያሉ ዋናው የመበስበስና የጥገኛ መንገድ ገብተው ነበር ተሃድሶ ሲጀመር የተሃድሶ ጉዞ ለማደናቀፍ ሞክረው ስላልተሳካላቸው በሰማእታት ስም እየተለመኑ ***የድርጅቱ መድረክ ረግጠው ሲወጡ ያው ቦታቸው የጥገኛው ጎራ እንደሆነ ግልፅ ነበር፣ ስለዚ እነዚህ ወገኖች የጊዜ ና የቅደም ተከተል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ገሚሱ በጠራራ ፀሃይ ገሚሱ ጨለማን ተገን በማድረግ ወደ ጥገኛው ካምፕ መግባታቸው አይቀርም ኣሉ፡፡*** በዚህ መሰረት ክቡር መሪው እንዳሉት አፈንጋጮቹ ተራ በተራ ወደ ትምክህቱና ጠባብነት ካምፕ ይቅርታ ጠይቀው ሲገቡ፣ ***መወሰን ወይም መድፈር አቅቷቸው መንታ መንታ እያሰቡ ለ15 ዓመታት ገባ-ወጣ ሲሉ የቀሩትን የመጨረሻዎቹ አሁን እንደ ፊተኞቹ ይቅርታ ጠይቀው ወደ ትክክለኛ ቦታቸው ዘው ብለው ሲገቡ አየናቸው፡፡*** እነዚህ ኣዳዲስ ገቢዎች ***(አሁን ባለፉት ቅርብ ወራት ወደ ፖለቲካው ዓለም የተቀላቀሉ የቀድሞ ሜጀር ጀነራል እና ሌተናን ጀነራል ማለቴ ነው)*** ሁለቱም ያሉትን ነገር በጣም ካስገረመኝ ጥቂት የግሌን ትዝብት ላካፍልና ወደ ዋናው ቁምነገሬ እመለሳለሁ፡፡ ትዝብቴን ትንሽ ልጥቀስ፡-

አንዱ ያለው "እኔ ከትግራይ ህዝብ የትጥቅ ትግሉ አንድ አካል መሆኔ እኮራበታለሁ"፣ በሌላ በኩል ደግሞ ህዝባዊ ወገንተኝነት ይዞ ከተታገለ ታጋይ የማይጠበቅ እንዲህ ሲሉ አነበብኩ እሱም ***"የመመረቂያ ፅሁፌን ከፃፍኩ ቦሃላ ኣሰብ በሰላም ካልተቻለ በሃይል ማስመለስ ኣለብን የሚል ኣቋም ያዝኩ ማለቱ"*** ሌላው የገረመኝ ስለ ዴሞክራሲ ሲናገሩ ***"በኔ አመለካከት፣ ኢህአዴግ አሁን ህገ-መንግስቱንም እየሸረሸረ ነው፡፡ ህገ-መንግስቱን በተሟላ መንገድ ተግባራዊ እያደረገ አይደለም፡፡"*** ለዚህ ደግሞ የሚካሄዱ ምርጫዎች ማሳያ ናቸው ይሉና፡-

- በ1997 ምን አይነት ሁኔታ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ህዝቡ እድል ሲያገኝ ማንን እንዴት እንደሚመርጥ ያሳየበት ምርጫ ነበር፡፡
- በ2002 ዓ.ም 96.6 በመቶ ነበር ገኘው ፓርቲ ያሸነፈው፡፡
- በ2007 ደግሞ መቶ በመቶ ሆኗል፡፡ ስለዚ 100% ማሸነፍ ካለ ዴሞክራሲ የለም አሉ፤

ከአንድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ዓላማ ይዞ የታገለ ታጋይ ለዛውም አመራር የነበረ ዴሞክራሲ በውጤት ለክቶ እንዲህ ማለቱ ገረመኝ፡፡ *ከዚህ መረዳት የሚቻለው በጀነራሉ አባባል የተዋጣለት ዴሞክራሲ የሚባለው 50% በ 50% ሲኖር ብቻ እንደሆነ ነው፤* በጣም ይገርማል፡፡

ሌላው አሁን በቅርቡ በዓይጋ ፎረም የወጣው ፅሁፍ ደግሞ ሌ/ጀነራሉ እንደ ፊተኞቹ መታገሌ ቅር ኣይለኝም ይሉና ግን ደግሞ *የሽግግር መንግስት መከላከያ ሰራዊት በዛን ጊዜ እሳቸው ይመሩት በነበረበት ጊዜ የኦነግ ሰራዊት ሰለማዊ የትግል መንገድ ረግጦ የፀረ ህዝብና የፀረ ሰላም መንገድ በመምረጥ በበደኖና በተለያየ አከባቢዎች ህዝብ ሲጨፈጭፍ ከቆየ ቦኋላ ሌ/ጀነራሉ የሚመሩት የመከላከያ ሰራዊታችን አኩሪ ታሪክ መስራቱ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለጥገኛ ኪራይ ሰብሳቢ ካምፕ እንደ ይቅርታ ጥያቄ እንዲታሰብላቸው ሌ/ጀነራሉ ያቀረቡት ሂስ* "ከኦነግ ጋር የነበረን ቅራኔ አፈታት ችግር ነበረው" ኣሉ፡፡ በጣም ይገርማል *ለካ ከኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ያፈነገጠ ሁሉ ልክ ከአንድ ወንዝ እንደተቀዳ መጀመሪያ የወጣውም መጨረሻ የወጣውም ሁሉም አንድ ነው* ኣልኩኝ፡፡

- የሌ/ጀነራሉ መነሻ ሓሳብ ገዢው ፓርቲ ሕገ-መንግስቱ የተዋጣለት ቢሆንም ሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተሟላ ሁኔታ እየተተገበረ ኣይደለም ኣሉ (የነዚህ መብቶች መጣስ በአስረጅ የቀረበ ነገር ባይኖርም)፡፡
  - መንግስት የዴሞክራሲ ምህዳሩ እያጠበበው ነው፣
  - አሁን መንግስት ችግር መኖሩ እየገለፀ ነው፣ *የችግሩ ሁኔታ ሲገልፁ ከፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓቱ አወቃቀር የሚነሳ ስርዓታዊ ችግር (Systemic Problem) ነው ብለው እርፍ አሉ፡* ለችግሩ መፍትሂ ብለው ያስቀመጡት በጣም በሚገርም ሁኔታ፡-
    - ቃል በቃል ባይሉትም ማንኛውም የትምክህትና የጠባብ ኋይሎች እንደሚሉት *ብሂራዊ ዕርቅ ይደረግ የሽግግር መንግስት ይቋቋም በአጭር ጊዜ የውጭ ታዛቢዎች ባሉበት ምርጫ ተካይዶ* ሁሉም የምርጫው ውጤት በፀጋ ይቀበል ኣሉን ፡፡

***"ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም" ሲሉ እንዲህ ነው***

***አንድ ያልተመለሰልኝ ጥያቄ ሁለቱ ጀነራሎች 15-ዓመት አድፍጠው ከቆዩ ቦኋላ ለምን ጊዜው አሁን ተመረጠ? በዛን ጊዜ ዴሞክራሲያዊ መብት ስላልተከበረ እንዳንል አንጃው ድርጅት መስርቶ መንቀሳቀስ ጀምሮ ነበር፣ አሁን ደግሞ የዴሞክራሲ ምህዳሩ ጠቧል እያሉ ያላቸውን ስሜት ያለምንም ስጋት እየዘከዘኩት ነው ግራ ያጋባኝ ይህ ነው፡፡*** ትዝብቴ ይህን ካልኩ ወደ ዋናው መልዕክቴ ልግባ፡፡

እውን ኣሁን በኢትዮጵያ የሚታየው ችግር ከፖለቲካዊ ስርዓቱ ኣወቃቀርና የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚነሳ ስርዓታዊ (Systemic) ችግር ነው? የሚለውን ቁልፍ ጥያቄ ለመመለስ እየተከተልነው ያለ ስርዓት ምንድነው? ምን አማራጮችስ አሉ? በኔ አመለካከት አሁን በኢትዮጵያ የሚታዩ ችግሮች መንስኤው ምንድነው መፍትሂውስ የሚለው ነገር በተለይ በቅርቡ በኦሮሚያና በጎንደር አከባቢ በተነሱት ሕገወጥ ሰልፎችና ዝርፊያዎች መነሻ በማድረግ አስተማሪና ለአገርና ለህዝብ የሚጠቅም ያልኩትን ከዚህ ቀጥሎ አቀርባሎ፡፡ በዚህ ኣጋጣሚ ለሁለቱ ጀነራሎች በትግላቸው ያረጋገጡትን ዴሞክራሲያዊ መብታቸው ተጠቅመው ይጠቅማል ያሉትን ሃሳብ መስጠታቸው እያደነቅኩ፣ አሁን እየሰጡን ያለ ሃሳብም ኣማራጭም አፍራሽና ህዝባዊ ወገንተኝነት የሌለው የጥገኞችና የኪራይ ሰብሳቢዎች መንገድ በመሆኑ አጥብቄ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እታገለዋለሁኝ እያልኩ፣ ሁለቱ ጀነራሎች አሁን ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ያፈነገጡ ቢሆኑም፣ በመራራው ትጥቅ ትግል ወቅትና በኤርትራ ወረራ ላይ ከተራ ታጋይነት እስከ ከፍተኛ ኣመራርነት ሆነው ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከልቤ የመነጨ ኣድናቆትና አክብሮት ያለኝ መሆኑ ስሜቴን መግለፅ እወዳሎ፡፡

## 2 አሁን በዓለማችን ያለ የኢኮኖሚ ስርዓት አማራጭ

ባለፈው 5ኛ አገራዊ የምጫ ቅስቀሳ እየሰማናቸው የነበሩ ኣማራጮች ሶሻል ዴሞክራሲ፣ ሊበራል ዴሞክራሲ እና ልማታዊ ዴሞክራሲ ናቸው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረቡት ኣማራጭ ሊበራል እና ሶሻል ዴሞክራሲ ሲሆን ኢህአዴግ ያቀረበውና በተግባር እየተከተለው ያለው ደግሞ ልማታዊ ዴሞክራሲ ነው፡፡ ታድያ የነዚህ ርእዮተ ዓለም ኣንድነትና ልዩነት ምንድ ነው? በኢትዮጵያ ያላቸው ማሕበራዊ መሰረት ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች መመለስ ና መገንዘብ ለዋናው ጥያቄ ***"እውን ኣሁን በኢትዮጵያ የሚታየው ችግር ከፖለቲካዊ ስርዓቱ ኣወቃቀርና የኢኮኖሚ ሁኔታ የሚነሳ ስርዓታዊ (Systemic) ችግር ነው?"*** ኣስፈላጊ ነው ብየ በማመን ይህን ለማቅረብ ፈለግኩ፡፡

በዓለማችን የታዩ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ እነሱም

1. ገበያ መር ኢኮኖሚ እና
2. የዕዝ ኢኮኖሚ ናቸው፡፡

***ገበያ መር ኤኮኖሚ*** ደግሞ በመሰረቱ የሸቀጦች ዋጋ መወሰን ያለበት በትእዛዝ ወይም በመንግስት ሳይሆን በኣቅርቦትና ፍላጎት መመጣጠን መሰረት በገበያው መወሰን ኣለበት የሚል ነው፡፡ ይህ ርዕዮት ደግሞ ኣሁን በዓለማችን በስፋት የምናየው ነው፡፡

***የዕዝ ኢኮኖሚ*** የሸቀጦች ዋጋ መወሰን ያለበት በገበያ ፍላጎትና ኣቅርቦት መሰረት ሳይሆን በትእዛዝ ወይም በፖለቲካዊ ውሳኔዎች ከኣንድ ማዕከል በሚወርድ መመሪያ መሰረት መወሰን ኣለበት ይላል፡፡ በዚህ መሰረት አገራችን ኢትዮጵያ ጨምሮ የሶሻሊስት ርዕዮት የሚከተሉ የነበሩ አገሮች ይጠቀሙበት የነበረና ሂዶ ሂዶ ልማትና ዕድገት በተፈለገው ደረጃ ማምጣት ስላልቻለ ብቻ ሳይሆን ውድቀትን ስላስከተለ አገሮች እርግፍ አድርገው ትተውታል፡፡

በዚህ መሰረት በአገራችን ኢትዮጵያ እየተተገበረ ያለው ልማታዊ ዴሞክራሲ (Democratic Developmental State) ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንደ አማራጭ እያቀረብዋቸው ያሉትን ሊበራል ዴሞክራሲ Liberal Democracy, ሶሻል ዴሞክራሲ Social Democracy, እንዲሁም ኒዮሊበራሊዝም Neo-liberalism በሙሉ የገበያ መር ኢኮኖሚ የሚከተሉ ርዕዮቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በሃገራችን ያሉ በሙሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያቀረብዋቸው ኣማራጮች እና ኢህአዴግ የሚከተለው ልማታዊ ዴሞክራሲ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ***ሁሉም የነፃ ገበያ መር ኢኮኖሚ የሚከተሉ መሆናቸው ነው፡፡*** ባለፈው 5ኛ አገራዊ ምርጫ ከቀረቡት አማራጮች አንድም ከነፃ ገበያ መርህ ውጭ አልነበረም፡፡ ስለዚህ በአገራችን በመተግበር ላይ ያለውን ***የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መርህ የማይቀበል የለም ብሎ ማደማደም ይቻላል፡፡ ልዩነታቸው ታድያ ምንድነው? የሁሉም ልዩነት የመንግስት ጣልቃ ገብነት መጠን ላይ ነው፡፡***

የዕድገት አመጣጡ ሲታይ መጀመሪያ ሊበራሊዝም Liberalism, ቀጥሎ ሶሻል ዴሞክራሲ Social Democracy እና ዌልፌር-ስቴት welfare-state ቀጥሎ ኒዮሊበራሊዝም Neo-liberalism ሲሆኑ ሁሉም በሊበራል ዴሞክራሲ ስር ሊጠቃለሉ ይችላሉ፡፡ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች አሁን በመታየት ላይ ያለው ደግሞ ልማታዊ መንግስት Developmental State በኛ ሁኔታ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት Democratic Developmental State ተብሎ የሚጠራ ነው፡፡ በሊበራል ዴሞክራሲ እንደ ቅደም ተከተሉ የመንግስት ጣልቃ ገብነት

እየቀነሰ የሚመጣ ሲሆን በልማታዊ መንግስት ግን ጣልቃ ገብነቱ የሰፋ ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ ርዕዮት ስንመለከት፡-

## 2.1 ሊበራሊዝም

ሊበራሊዝም በዋናነት ከኢነዱስትሪ አብዮት ዘመን ጀምሮ የባለሃብቱን መብት የሚያስጠብቅ እና የሁሉም ርዕዮቶች መነሻ ሆኖ፤ መንግስት በተወሰኑ በታላላቅ የኤኮኖሚ ኣውታሮችን ተቆጣጥሮ በነፃ ገበያ መርህ የሚያንቀሳቅሳቸው ሁኔታ የነበረ ሲሆን ይህም ***እስከ 2ኛ የዓለም ጦርነት ማግስት በዓለማችን የአስተሳሰብ ልዕልና ተጎናፅፎ የነበረና በዓለማችን ከፍተኛ ዕድገት ለማምጣት ችሎ የነበረ ሲሆን በስተመጨረሻ የድሃውና የሃብታሙ ልዩነት እጅግ በጣም የሰፋ በመሆኑ ማሕበራዊ ቀውስና ምስቅልቅል በመፈጠሩ ሶሻሊዝም እንዲፈጠር እና ሁለተኛ የዓለም ጦርነት የተቀሰቀሰበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡*** ከ2ኛ የዓለም ጦርነት ቦሃላ በሊበራሊዝም የተፈጠረውን ቀውስና ማሕበራዊ ምስቅልቅል መፍትሂ ሊሰጥ ይችላል በሚል በዓለማችን በተለይ ባደጉት ኣገሮች የሶሻል ዴሞክራሲና የዌልፌር ስቴት ርዕዮቶች ከራሱ ሊበራሊዝም ተወለዱ፡፡

***የተፈጠረውን ማሕበራዊ ቀውስ ለመፍታት ከባለሃብቱ ዳጎስ ያለ ግብር በመሰብሰ የህብረሰሰቡን ችግሮች የሚፈቱ መሰረተ-ልማቶች፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የውሃ ወዘተ ኣቅርቦቶች በዝቅተኛ /በተደጎመ/ ዋጋ ለህብረተሰቡ እንዲያቀርቡ፣ የሶሻል ዴሞክራሲ የሰራ ሲሆን፣ የዌልፌር ስቴት ኣስተሳሰብ ከሶሻል ዴሞክራሲ በመሰረቱ ኣንድ ሆኖ ዌልፌር-ስቴት ከሶሻል ዴሞክራሲ በበለጠ ዳጎስ ያለ ግብር ከባለ ሃብቱ በመሰብሰብ የኣኗኗር ስታንዳርድ በማውጣት ለዜጎች በተለይ ስራ ለሌላቸው ወርሃዊ ድጎማ የሚያደርግበት ሪዕዮት ነው፡፡***

እነዚህ የተፈጠሩትን የሶሻል ዴሞክራሲና የዌልፌር ስቴት ኣስተሳሰቦች ተፈጥሮ የነበረውን ማሕበራዊ ቀውስ በመፍታት ኣሁንም ባደጉ አገሮች የተረጋጋና የበለፀገ ኢኮኖሚ በመፍጠር ከ30 ዓመት በላይ ልዕልና ኣግኝተው ዘልቀዋል፡፡ በመጨረሻም በተለይ በ1973 እ.አ.አ. ጀምሮ በነዳጅ ዋጋ መጨመር የጀመረ ማሕበራዊ ቀውስ መፈጠር ጀመረ፣ የዓለም ኢኮኖሚ ዕድገትም መቆም ጀመረ፡፡ ***የዚህ ሁሉ ምክንያት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ነው፣ ስለዚ ሁሉም ነገር ለግሉ ባለሃብት በመተው መንግስት በህግና ስርዓት ማስከበር፣ ዳርድንበር ማስከበር ብቻ መስራት ኣለበት ተባለ፡፡*** መንግስት ወደዚህ በመግባቱ ውድድሩን እንዳይፋፋም እና ዕድገት እንዳይመጣ ዕንቅፋት ሆኖዋል የሚል በኣሜሪካና ኢንግሊዝ ምሁራን የተጀመረውን ኣስተሳሰብ በነ የኢንግሊዝዋ ማርጋሪታቸርና የኣሜሪካው ሬጋን መተግበር የተጀመረው፣ **ቀስ በቀስ በዓለማችን አስተሳሰቡ ገነነ የበላይነት እንዲጎናፀፍ ቻለ**

**ይህም እስከ አሁን ድረስ በዓለማችን ገኖ ያለውን ኒዮ-ሊበራሊዝም ነው፡፡** ይህ ኣስተሳሰብ ዓለማችንን ለመቆጣጠር *The Washington Consensus* የሚባለው በቅፅል ስሙ ***የኒዮ-ሊበራሊዝም ዓስርቱ ትእዛዛት (Ten Commandments of Neoliberalism)*** እየተባለ የሚጠራው መስፈርቶችን በማውጣት ከዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅት ዕርዳታም ብድርም የሚፈልግ ሁሉ እነዚህን መስፈርት የማሟላት ግዴታ ተጣለ፡፡ በዚህ መሰረት ኣሁንም በዚህ ርዕዮት ከ1980 ጀምሮ እስከ 2000 መጀመሪያዎች **ዓለማችን ዓይታው የማታውቅ ከፍተኛ ዕድገትና ስልጣኔ የተመዘገበበት ሁኔታ የተፈጠረ ሲሆን፣ የነፃ ገበያው ኢኮኖሚው ልቅ ሂዶ ላለው ይጨመርለታል እንደሚባለው ሁሉ፣ ሃብታሙ የበለጠ ሃብታም ሲሆን ኣብዛኛው ህዝብ ግን በድህነትና በብድር የሚማቅቅበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡** ከ2000 እኤአ መጀመሪያዎች ጀምሮ ዕድገቱ የድሃውና የሃብታሙ ልዩነት አሁንም እጅግ በጣም የሰፋ ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ በዓለማችን በጣም ጥቂት ቢሊየነሮችና በጣም እጅግ ብዙ ድሃ የተፈጠረበት ዓለም ሆኖ ይኸው ማሕበራዊ ቀውስ የበዛባትና ግጭቶች በብዛት እየታየ ያለባት ዓለም፣ በየቀኑ በሽብርና በጦርነት ምክንያት ህዝብ የሚያልቅባትና የሚሰደድባት፣ ዓለም ሆና ትገኛለች፡፡ ***በተለይ በ2007 እአአ በተፈጠረው የፋይናንስ ቀውስና እሱን ተከትሎ በመጣው የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከተለውን ማሕበራዊ ቀውስ መጀመሪያ ያደጉ አገሮችን ኩፍኛ የመታ ሲሆን ቀስ በቀስ ለሁሉም የተረፈና አሁን ድረስ እየታዩ ያሉ አለመረጋጋቶችን ምክንያት እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡*** ***በዚህ ቀውስ ኩፍኛ የተመቱ አገሮች ቀድሞ ኒዮሊበራሊዝም ያስተጋቡና የርእዮቱ ዋና አቀንቃኞች የሆኑትን አገራት ሲሆኑ፤ ብድርና ዕርዳታ ለማግኘት ሳያቅማሙ የኒዮ-ሊበራሊዝም ዓስርቱ ትዕዛዛት የተቀበሉትን አገሮች በጣም ጎድቷቸዋል፡፡*** የኒዮ ሊበራሊዝም አቀንቃኞች ለቀውሱ እንደ ማስታገኛ የወሰዱት ነገር ቢኖር፣ ያ ያኔ ይህ ርዕዮት ሲጀምሩት የተፀየፉትን የመንግስት ጣልቃ ገብነት ነበር፡፡ የአሜሪካም ሌሎች የአውሮፓም መንግስታት የተፈጠረውን የኢኮኖሚ ቀውስ ለማስታገስ ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ ጎልተው የሚጠቀሱት መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ በመግባት በመቶዎች ቢልዮን የሚቆጠር ዶላር መደጎም ነው፡፡ **ይህ ማስታገሻ ከመሆን የዘለለ መሰረታዊ መፍትሄ ስላልሆነ እነሆ በዓለማችን እየታየ ያለው ምስቅልቅል መልኩን እየቀየረ እንደቀጠለ ነው፡፡ ወቅቱ እንደ ወትሮው መሰረታዊ መፍትሄ የሚያመጣ ርእዮት ካደጉ አገራት ይጠበቃል፡፡ አንዱ በእርግጠኝነት መናገር የሚቻለው ግን ኒዮ-ሊበራሊዝም ዕድሜዉን ጨርሿል፡፡** **ይህ ርዕዮት ለማንም (ላደጉ አገራትም በማደግ ላይ ያሉ አገራትም) የማይጠቅም፣ ድህነትን ያባባሰ፣ ጥቂቶችን በሃብት ላይ ሃብት ሲያደርግ ህዙኋኑ ወደ ባሰ ድህነት ያስገባ መሆኑ አሁን እያየነው ያለ ሓቅ ነው፡፡**

## 2.2 ልማታዊ መንግስት

የልማታዊ መንግስት ርዕዮት በደንብ ተተንትኖ የቀረበ ነገር ባይኖርም በተግባር ግን ተተግብሮ ፈጣን ውጤት የተመዘገበበት ርዕዮት መሆኑ እንደነ ኮርያ፣ ታይዋን፣ ሲንጋፖር፣ ቻይና፣ ወዘተ ብዙ ኣብነቶች መጥቀስ ይቻላል፡፡ እንደነዚህ አገሮች ቀድመን የጀመርነው ባይሆንም በጣም በአጭር ጊዜ ቢሆንም አገራችን ኢትዮጵያም *ይህን ርዕዮት በተገበረቻቸው 13 ዓመታት ያሳየን ሓቅ ቢኖር ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው መላው ዓለም የመሰከረው ዕድገት ማስመዝገባችን ነው፡፡*

የልማታዊ መንግስት ርዕዮት መሰረቱ የነፃ ገበያ ሆኖ ከሌሎች የሊበራሊዝም ኣስተሳሰቦች (ከሶሻልዴሞክራሲና ዌልፌር ስቴት ኣስተሳሰብ) የሚለየው በኢኮኖሚው የመንግስት ጣልቃ ገብነት መጠን ነው፡፡ የልማታዊ መንግስት ርዕዮት የሚለው ልማት የህልውና ጉዳይ አድርጎ በመውሰድ ልማትን ለማፋጠን የልማት ማኖቆዎች መፈታት፣ የገበያ ጉድለቶች መሟላት አለባቸው የሚል ጠንካራ ዕምነት በመያዝ ይህን ለመፍታት የመንግስት ሚና ወሳኝ ነው ብሎ ያምናል፡፡ *እነዚህን ጉድለቶች ለመሙላት ለግል ወይም ለመንግስት ተብሎ ድንበር ሳይበጅለት ባፋጣኝ በመሙላት ዕድገቱን ማፋጠን ይላል፡፡* በመሆኑም ለባለሃብቱ ሰፊ ዕድል በመስጠት እንዲንቀሳቀስ ሲያደርገው ባለ ሃብቱ ሊሞላው ያልቻለ ጉድለትና ዕድገቱን የሚጠይቀው ክፍተት መንግስት እንዲሞላና ዕድገቱ እንዲቀጥል የሚያደርግ ርዕዮት ነው፡፡ ስለዚህ ልማታዊ መንግስት በነፃ ገበያ ህግጋት በስፋት እና በተመረጡ መስኮች የመንግስት ጣልቃ ገብነት መኖር አለበት ይላል፡፡

## 2.3 መሰረታዊ ልዩነቱ ምንድን ነው?

የልማታዊ መንግስት ርዕዮት የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሲል የኣገር ልማት ከማፋጠን እና ከዚህ ልማት ህዝቡ ፍትሃዊ ተጠቃሚ ከማድረግ ነው፣ ህዝቡ የጎን ተመልካች ሆኖ ድጎማ የሚጠብቅ ማድረግ ሳይሆን ህዝቡን በሙሉ ዓቅሙ በልማቱ ተሳታፊ እንዲሆንና በተሳተፈው መጠን ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ለዚህም ህዝቡ በልማት ሰራዊትነት በማደራጀት በገጠሩም በከተማም የልማት ስራዎች በተደራጀ ኣኳሃን እንዲንቀሳቀስ በማድረግ፣ እዚህ ላይ የሚያጋጥሙ ጉድለቶች እንደ የማስፈፀም ዓቅም፣ ግብአቶች፣ ቴክኖሎጂዎች፣ አሰራሮች፣ መሰረተ-ልማቶች ወሰዘ መንግስት በስፋት እንዲሞላ የሚያደርግ ርዕዮት ነው፡፡ የሚፈጠሩ ማሕበራዊ ቀውሶች በዘለቄታው መፈታት የሚችሉት ማሕበረሰቡ በቀጥታ በልማቱ እንዲሳተፍ ሁኔታዎች በማመቻቸት እንጂ ማስታገሻ (ድጎማ) በመስጠት ኣይደለም ብሎ

ያምናል፡፡ ለዚህም ነው ልማታዊ መንግስት ወገንተኝነቱ ለሰፊው የከተማ ና የገጠሩ ህዝብ ነው የሚባለው፡፡

የሊበራል አስተሳሰቦች የመንግስት ጣልቃ ገብነት ሲሉ በህዝቡ የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄ ምክንያት የሚፈጠረው ቀውስ፣ ዓመፅ፣ ብጥብጥ፣ አለመረጋጋትና ነውጥ ምክንያት ሊደርስ የሚችለው የባለሃብቱ ንብረትና ሃብት ውድመት ለማስወገድ ሕብረተሰቡን ከልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል፣ ህብረተሰቡ ከልማቱ ተጠቃሚ ከሆነ ዓመፅ፣ ነውጥ፣ ብጥብጥ፣ የሚባል ነገር አይኖርም ካለም በጣም ጥቂትና ከቁጥጥር ውጭ ሊሆን አይችልም ይላል፡፡ ***ስለዚህ የኢኮኖሚው ሞተር ዋና አንቀሳቃሽ በከተማም በገጠርም ባለሃብት በመሆኑ፣ ባለሃብትም ከሚያገኘው ትርፍ ለሕብረተሰቡ ማሕበራዊ አገልግሎቶችና ለማሕበራዊ ዋስትና ተግባራት የሚውል ተጨማሪ ግብር እንዲጫን በማድረግ በድጎማ መልክ ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ያምናል፡፡*** ለዚህም ነው የሊበራሊዝም አስተሳሰቦች በሙሉ ውግንናቸው ለከተማውና ለገጠሩ ባለሃብት ነው የሚባለው፡፡

## 2.4 ከልማቱ የዜጋ/ህዝብን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ

አገራችን ጨምሮ በዓለማችን ድህነት፣ ሃላቀርነትና ብሶት የወለደው ግጭቶች፣ ማሕበራዊ ምስቅልቅል፣ እንዲሁም የፍትሃዊ ተጠቃሚነት ጥያቄን መሰረት በማድረግ የሚነሱ በርካታ ዓመፆች ነውጦች ሲነሱ ተስተውሏል፡፡ የነዚህ አለመረጋጋት መፍታት የሚቻለው ሁለቱም አመለካከቶች (ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስትና ሊበራል አስተሳሰቦች) የሚስማሙበት ነገር ቢኖር ህዝቡ/ዜጋው ከልማቱ ተጠቃሚ በማድረግ እንደሆነ ይስማሙበታል፡፡ ታድያ ልዩነቱ የት ነው -- ***ልዩነቱ እንዴት ከልማቱ ተጠቃሚ ይሆናል?*** የሚል ላይ ነው፡፡ ፡-

- በሊበራሊዝም አቀንቃኞች ዜጋው ከልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ አለብን ሲሉ መነሻው ***የግል ባለሃብቱ ንብረት እንዳይዘረፍና መብቱ እንዳይጣስ ከሚል መነሻ ሆኖ፣*** ዜጋው ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው ባለሃብቱ (የስርዓቱ ዋነኛው ባለቤት) በሚፈጥርለት የስራ ዕድል እና/እንዲሁም ከባለሃብቱ ደጎስ ያለ ሃብት በማሰባሰብ በድጎማ መልክ ማከፋፈል (ነፃ ወይም በዝቅተኛ ዋጋ ትምህርት፣ ጤና፣ ውሃ፣ ትራንስፖርት፣ መጠለያ፣ ወዘተ መሰረታዊ ፍላጎቶች ማቅረብ) ይላል፡፡
- አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን ግን ***ህዝቡ ከልማቱ ተጠቃሚ መሆን አለበት ሲል ለህዝብ ካለው ወገንተኝነት የሚነሳ ሲሆን፣*** ህዝቡ ከልማቱ ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻለው ድጎማ በመስጠትና የልማቱ የጎን ተመልካች

በማድረግ ሳይሆን ህዝቡ በልማቱ በቀጥታ ተሳታፊ በማድረግ በተሳትፎው መጠን ተጠቃሚና የስርዓቱ ባለቤት በማድረግ ነው ይላል፡፡ ***ህዝቡ ከስርዓቱ ተጠቃሚ ለማድረግ ደግሞ በተደራጀና ልማታዊ ሰራዊት በመፍጠር ማንቀሳቀስ እንዳለብን ያስቀምጣል፡፡*** በተደራጀ መልኩ ከተንቀሳቀሰ መንግስት ያለበትን ችግሮች (የገበያ ጉድለቶች በመሙላት ያግዛል፡፡)፡፡

## 2.5 በዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጥያቄ ያለው አንድነትና ልዩነት

**ሊበራሊዝም ከመነሻው ለግል ባለሃብት የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ያተኮረ ሊበራል ኢኮኖሚ መፍጠር እንጂ የብዙኋኑ ዴሞክራሲ ከማስፈን አኳያ ትኩረት የሚሰጥ አልነበረም እንዲያውም የመምረጥና የመመረጥ ዕድል በማጥበብ ለባለሃብት ብቻ እስከ መገደብ የተኼደበት ሁኔታ ነው የነበረው፡፡** በሂደት ግን እነዚህ መብቶች ቀስበቀስ እየተረጋገጡ መጡ፡፡ ለምሳሌ የጥቁሮች የመምረጥና የመመረፅ መብት፣ የሴቶች የመምረጥና የመመረጥ መድት፣ ሃብት ያለውም የሌለውም የመምረጥና የመመረጥ መብቶች በሂደት ዘግይተው የተከበሩበት ሁኔታ ነው የነበረው፡፡ ልማታዊ መንግስትም ተከታዮችም ቢሆን ዋናው ትኩረት ድህነት ማጥፋት፣ ሃብት ማካበትና ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ዕድገት ማስመዝገብ እንጂ ዴሞክራሲ ማስፈን እንደ ዓላማ ይዞ የተንቀሳቀሰ አንድም ሃገር ኣልነበረም፡፡ በሂደት ግን ዴሞክራሲያዊ ሊባል የሚችል ስርዓት ለመገንባት በቁ፡፡

ከዚህ ሓቅ በመነሳት ዘግይተውም ቢሆን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመፍጠራቸው በዴሞክራሲ ያለውን አመለካከት በሁለት ከፍለን ለማየት እንሞክራለን፡፡ እሱም ልማታዊ ዴሞክራሲና ሊበራል ዴሞክራሲና ናቸው፡፡ ***ልማታዊ ዴሞክራሲ ስንል በኢኮኖሚ መስክ የልማታዊ መንግስት ርእዮት የሚከተል ሲሆን ከኢኮኖሚ ዕድገት ጎንለጎን ከጅምሩ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ዓልሞ ስለሚንቀሳቀስ ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ርእዮት ብለን እንጠራዋለን፡፡*** ኢህአዴግ የሚከተለው ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ በኢኮኖሚ ስርዓቱ የልማታዊ መንግስት ርእዮት በመሆኑ ልማቱም ዴሞክራሲም ሁለቱም በጋራ ለመገንባት የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት ርእዮት ወይም ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮት በማለት ልንጠራው እንችላለን፡፡ ***ስለዚ ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ስንል ልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት ማለታችን ነው፡፡***

የሊበራል ዴሞክራሲና የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮቶች ከሚያለያያቸው መሰረታዊ ጉዳይ አንዱ በዴሞክራሲያዊ መብቶች አከባበር ላይ ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ መብቶች በምንልበት ጊዜ የመሰለህን አመለካከት የማንፀባረቅ፣ የመፃፍ፣ የመቃወም፣ ሰለማዊ ሰልፍ የማድረግ፣ የመደራጀት የመናገር መብቶችን በሚል ሊጠቃለል ይችላል፡፡ የነዚህ ሁለት ርእዮቶች መሰረታዊ የልዩነት መነሻቸው እነዚህ የዴሞክራሲ መብቶችን በተጨባጭ መሬት ላይ በማውረድ ሆኖ እሱም በሁለት መሰረታዊ መብቶችን ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡ የግል ዴሞክራሲያዊ መብትና የቡዱን ዴሞክራሲያዊ መብት ብሎ ማየት ይቻላል፡፡ ዋናው ልዩነት ደግሞ በቡዱን መብቶች ላይ ነው፡፡

## 2.5.1 ሊበራል ዴሞክራሲ

በሊበራሊዝም ኣስተሳሰብ የሁሉም ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሰረት የግለሰብ መብት ነው የሚል እምነት ኣለው፡፡ ስለዚህ የግለሰብ መብት ያለምንም መሸራረፍ ከተከበረ ሌላ መብት ካለም የግለሰብ መብት በመከበሩ ብቻ በዛው ይከበራል ይላል፡፡ ይህ ርእዮተዓለም የቡድን መብት የሚባል ነገር ኣይቀበልም፡፡ የዚህ መነሻም የሊበራሊዝም ዋናው ዓላማ የግል ባለሃብት መብትን ማስከበር በመሆኑ፣ የግል ባለሃብት መብቱና ንብረቱ መጠበቅ የሚቻለው የግል መብቶች ሙሉ በሙሉ ሲከበሩ ነው ይላል፡፡ ***<u>የቡዱን መብት ጥያቄ ማንሳት ማለት በቡዱን መብት ስም ተደራጅቶ የባለሃብቱን ሃብትና ንብረት ለመዝረፍ የሚጠነሰስ ተንኮል ነው ብሎ ስለሚያምን የቡዱን መብት የሚል ጥያቄ ሲነሳ የሊበራል ተከታዮች ሲባንኑ ይኖራሉ፡፡</u>***

## 2.5.2 አብዮታዊ ዴሞክራሲ / ልማታዊ ዴሞክራሲ

ኢህአዴግ የሚከተለው የልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት መስመር መነሻው ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ኣስተሳሰብ ሆኖ በዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለው ኣቋም የግል መብትና የቡዱን መብት ያለምንም መሸራረፍ መከበር ኣለበት የሚል ነው፡፡ እንደ ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ ኣባባል ሁለቱም መብቶች የማይተካኩና የአንዱን መብት በማስከበር ብቻ የሌላኛው መብት ማስከበር ኣይችልም፡፡ ስለዚህ የግል መብትና የቡዱን መብት በእኩል ዓይን መታየትና መከበር ኣለበት የሚል የኣብዮታዊ ዴሞክራሲ የፀና ኣቋም ነው፡፡

***<u>በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አመለካከት፣ የግል መብት በማስከበር ብቻ ሊረጋገጡ የማይችሉ፣ ግን ደግሞ በተደራጀ ሁኔታ ከታገሉ ብቻ የሚረጋገጡ መብቶች ኣሉ ይላል፡፡ እነሱም ለመጥቀስ ያክል፡-</u>***

- የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ክልልህን የማልማት፣ በቋንቋህ የመናገር፣ የመማር፣ የመዳኘት፣ የራስን ባህል የማሳደግ፣ የራስን ዕድል የመወሰን መብቶች፤
- የፆታ እኩልነት የማረጋገጥ መብት
- በኋይማኖት ጉዳይ የመሰለህን እምነት የመያዝ መብት የግል መብት ቢሆንም ግን ደግሞ የጋራ እምነት ላይ በጋራ ፆሎትና ስብከት የሚደረግበት ቦታ የማግኘት መብት፣ በነፃነት እምነትን የማራመድና የመስበክ በእምነት ዙርያ በጋራ የመሰብሰብ መብት፣ የጋራ የመቃብር ቦታ የማግኘት መብት፤
- የሰራተኛ፣ የላባደር የመደራጀት መብት፣ የተጠቃሚነት ጥያቄ የማቅረብና መልስ የማግኘት መብት ወዘተርፈ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ እላይ የተዘረዘሩትን የጋራ ወይም የቡዱን መብቶች የግል መብት በመከበራቸው ብቻ የሚከበሩ አይደሉም ይላል፡፡ አብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ እነዚህ መብቶች በጋራ በመደራጀት ብቻ የሚረጋገጡ መሆናቸውና በአንድ ዴሞክራሲያዊ የሚባል ስርዓት ልዩ ቦታ ተሰጥቷቸው ከግል መብት ሳይደበላለቁ መቀመጥ ወይም መከበር ያለባቸው ናቸው የሚል ፅኑ እምነት ኣለው፡፡

__ትክክለኛ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚባለው ሁለቱም መብቶች (የግልና የቡዱን መብቶች) በእኩል ዓይን በማየት ያለምንም መሸራረፍ እንዲከበሩ የሚያደርግ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚለው ከነዚህ ሁለት የማይነጣጠሉ መብቶች አንዱን ብቻ ነጥሎ እውቅና በመስጠት የሚያከብር ስርዓት ሙሉ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ነው ብሎ ኣያምንም፡፡__

ከአገራችን ሁኔታ ሲታይ፣ ኢትዮጵያ ለዘመናት በዘውዳዊውና የደርግ የትምክህተኞች ስርዓት ህዝቦችዋ ሲሰቃዩ የነበሩ ህዝቦችና ብሄር ብሄረሰቦች አገር፣ የተለያዩ የአገር በቀልና የውጭ በርካታ እምነቶች የተቀበለች አገር፣ ለዘመናት ልዩነቶችን ማስተናገድ ተስኗት በእርስ በርስ ጦርነት ስትታመስ የነበረች አገር፣ ህዝቦችና ብሄር ብሄረሰቦች መብታቸው ለማስከበር በጋራም በተናጠልም ሲታገሉና መስዋዕት ሲከፍሉ የኖርባት አገር በመሆንዋ ለዚህኛው ፍቱን መድሃኒት የጋራ/ቡዱን መብቶችና የግል መብቶች ሳይነጣጠሉ ማክበር ነው፡፡ እነዚህ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ደግሞ በሊበራሊዝም ሳይሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ብቻ ነው የሚከበረው፡፡ ***__ስለዚህ ነው ለኢትዮጵያ አገራችን ኣብዮታዊ ዴሞክራሲ የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ለዘመናት የታገሉለትን የቡዱን__***

መብቶች የሚያስከብርና ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነትዋ አስጠብቃ እንድትቀጥል የሚያደርግ ብቸኛው ርእዮት ነው፡፡

# 3 እነዚህ ኣማራጭ ርዕዮቶች በኢትዮጵያ ያላቸው ማሕበራዊ መሰረት ምን ይመስላል?

በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሲታይ የሊበራል ኣስተሳሰቦች በሙሉ እንዳየናቸው ከሁለት መቶ ዓመታት በፊት የዴሞክራሲ ሀ፣ ሁ ሲጀመር ጀምሮ እያደገና እየተጠናከረ የመጣ ጠንካራ የባለሃብት ድጋፍ ያለበት ኣስተሳሰብ እንደሆነ ማይት ይቻላል፡፡ ይህ ባለሃብት በጠንካራ የገበያ ህግጋት ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ፣ የነፃ ገበያ ህግጋት ዋናው የህልውናው መሰረት ኣድርጎ የሚንቀሳቀስ፣ ይህ ነፃ ገበያ ህግጋት በኣገሩ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም ሳይሸራረፍ እንዲተገበር ጠንክሮ የሚሰራ በዓለም ደረጃ ካሉት ኣምሳያዎቹ እየተናበበ የሚንቀሳቀስ ሃይል ነው፡፡ የሊበራሊዝም ኣስተሳሰብ የዕድገት ደረጃው ሲታይ ከቅድመ የኢንዱስትሪ አብዮት ጀምሮ ሶሻል ዴሞክራሲና ዌልፌርስቴት ብሎ ኣሁን ኒዮ-ሊበራሊዝም ሆኖ የዓለማችን ሃብቱም ስልጣኑም ተቆጣጥሮ የሚገኝ ርዕዮተ-ዓለም ነው፡፡ በ200 እስከ 250 ዓመታት ውስጥ እዚህ የዕድገት ደረጃ ሊደርስ የቻለው የነበሩትን የገበያ ጉድለቶች መሙላት በመቻሉ ነው፡፡ የገበያ ጉድለቶች መሙላት በመቻሉ ነው ሲባል ደግሞ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፣ የሰለጠነ የሰው ሃይል ኣቅርቦት፣ የበለፀገ የገበያ መረጃና ስርዓት፣ የስርዓቱ የአመለካከት የበላይነት መፍጠር በመቻሉ ነው፡፡ በዚህ ረጅም ጉዞ የመንግስት ጣልቃ ገብነት በኢኮኖሚው ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ፣ እየቀጨጨ እዚህ ኣሁን እምናየው ላይ ደርሷል፡፡ ስለዚ በዓለም ደረጃ ኣሁን እየተሸረሸረ ያለ ቢሆንም የበላይነቱ እንደያዘ ያለ፣ ጠንካራ የተደራጀና ረጅም ዕድሜና ተሞክሮ ያለው የዓለማችን ፈላጭ ቆራጭ የባለሃብት ርዕዮተ-ዓለም ነው፡፡

በኢትዮጵያ ደረጃ ሲታይ ግን በተገላቢጦሽ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለዘመናት የሃልዮሽ ጉዞ በመጓዝ ላይ የነበረች በመሆንዋ ከዓለማች ድሆች ድሃዋ አገር፣ ከዕርዳታ ውጭ መኖር ያቃታት ኣገር፣ በድህነት እየማቀቀች የኖረች ኣሁን በማንሰራራት ላይ ያለች አገር ናት፡፡ ከዚህ ኣኳያ ሲታይ የባለሃብት መብትና ነፃነት መጠበቅ የሚችል የተደራጀ አካል ወይም ፓርቲ የሌላት አገር ሆና የምትገኝ ናት፡፡ እንደ የበለፀጉ አገሮች ሁሉንም የገበያ ጉድለቶችን ተሟልተው ያለምንም የመንግስት ጣልቃ ገብነት መንቀሳቀስ ስለምንችል እንዲሁም ሁሉንም የህብረተሰቡ ፍላጎቶች በግሉ ባለሃብት ማሟላት ስለሚቻል ከመንግስት ጣልቃ ገብነት የፀዳ

***የነፃ ገበያ ስርዓይ መኖር አለበት የሚል አንድም የተደራጀ ሃይል የለም፡፡ የአገራችን የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲታይ በተቃራኒው ነው፡፡***

**አገራችን ከነበረችበት የኋልዮሽ ጉዞ ወጥታ አሁን በመነሳት/በማደግ ላይ ያለች አገር በመሆንዋ *ያለን ባለሃብት በሁለት እግሩ ቆሞ መሄድ የማይችል ገና በመንግስት እጅ ተደግፎ ዳዴ በማለት ላይ ያለ፣ መንግስት እጁን (ድጋፉን ወይም ባልቃ ገብነቱን) ካነሳ አንደ እርምጃ ሳይራመድ ተንገዳግዶ የሚወድቅ ጨቅላ ህፃን ነው ያለው፡፡* በአገራችን ከፍተኛ የገበያ ጉድለቶች በመኖራቸው ባለሃብታን በተሟላ አቅሙ መወዳደር አይችልም፡፡ ምክንያቱ ሰፊ የመሰረተ ልማት ጉድለት፣ ሰፊ የሰለጠነ የሰው ኋይል እጥረትና የተጠናከረ የምርምርና የስልጠና ተቋማት እጥረት፣ ሰፊ የቴክኖሎጂ ክፍተት፣ ሰፊ የትራንስፖርትና የኮሚኒኬሽን ጉድለት፣ ሰፊ የፋይናንስ አቅርቦት ጉድለት፣ ሰፊ የገበያ ትስስር ጉድለት ወዘተርፈ በጣም ሰፊ የገበያ ጉድለቶች እያሉ በዓለም ገበያ ተወዳድሮ ማሸነፍ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ሊበራሊዝብ በኢትዮጵያ ፈፅሞ፣ እደግመዋለሁ ፈፅሞ፣ ማህበራዊ መሰረት የለውም፡፡ *ማሕበራዊ መሰረት የሌለው የሊበራል ርእዮት ለመገንባት መመኮር ደግሞ፣ የርእዮቱ ቀንደኛ ጠላት የሆነው የኪራይ ሰብሳቢነት ስርዓት መገንባት ማለት ነው፡፡***

- ***መንግስት በአገሪቱ የሰለጠነ የሰው ኋይል ማቅረብ ካልቻለ፣ የአገራችን ባለሃብት የሰለጠነ የሰው ኋይል ከውጭ አገር በውጭ ምንዛሪ ገዝቶ ለመወዳደር አቅሙ የለውም፣***
- ***መንግስት የመሰረተ ልማት ካልዘረጋ የአገራችን ባለሃብት ይህንን የመዘርጋት አቅም የለውም ስለዚ መወዳደር አይችልም፣***
- ***መንግስት በዝቅተኛ ወለድ ብድር ካላቀረበ በገበያ በከፍተኛ ወለድ ብድር አግኝቶ መወዳደር አይችልም፣***
- ***መንግስት በዝቅተኛ ዋጋ ለኢንቨስትመንት መሬት ካላቀረበ፣ ባለሃብታችን በውድ ዋጋ መሬት በመግዛት ሊወዳደር አይችልም፣***
- ***ወዘተርፈ***

***ስለዚ ሰፊና የተመረጠ የመንግስት ባልቃ ገብነት የሚቀበል የልማታዊ መንግስት መስመር ለኢትዮጵያ ድሃው ህዝብ በልማቱ ተሳታፊ በማድረግ ከድህነት ወጥቶ የተሻለ ኑሮ እንዲኖር የማድረግ ዓላማ ያለው ብቻ ሳይሆን የአገራችን ባለሃብትም ለመወዳደር እንዲችል የመወዳደሪያ ዓቅም የሚገነባለትና በተቻለ ፍጥነት ዓቅም አግኝቶ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪ የሚያደርገው ወደር የሌለው አማራጭ ነው፡፡***

ስለዚህ ባለው ጉድለት ልክ በጣም ሰፊና በተመረጠ አኳኋን የመንግስት ጣልቃ ገብነት ከሌለ ባለሃብታችን ቶሎ ዓቅም አግኝቶ በዓለም ገበያ መወዳደር አይችልም፣ ህዝባችን የሚፈልገው ቶሎ ከድህነት የመውጣት ምኞት አይሳካም፡፡

**በርግጥ ለዚህ የገበያ ጉድለት የመሙላት ጥያቄ ሊበራሊዝም መልስ አለው፡፡** እሱም መንግስት እጁን ከሰበሰበ ጉድለቱ በባለሃብቱ ይሞላል የሚል ሲሆን መቼ የሚለው የጊዜ ጥያቄ ሲመልስ የቻለውን ትርፍ የሚያገኝበትን መስክ አሁን የተቀረው ደግሞ አቅም ሲያገኝ የሚል መልስ ነው የሚሰጠው፡፡ ***ሊበራሊዝም የገበያ ጉድለቶችን አይሞላም የሚል አመለካከት የለም ግን በጣም ዘገምተኛ ነው የሚል ነው ማከራከርያው፡፡ የአለማችን ልዕለሃያላንና በጣም ያደጉ የተባሉ አገሮች እዚህ ደረጃ የደረሱት በሊበራሊዝም መንገድ ከ200 ዓመታት በላይ ተጉዘው ነው፡፡*** **ታድያ በሚልዮኖች የሚቆጠር ህዝብ ከድህነት ወለል በታች የሚማቅቅ ህዝብ ያላት አገር፣ ቀልጣፋ ልማት ወይም ዕድገት የሞት ሽረት ጥያቄ በሆነበት አገር እንዴት ይህን መንገድ ይመረጣል?** ***በአገራችን በተቋዋሚ ጎራ መልስ ያጣ ጥያቄ፡፡***

ኣሁን በመነሳት ላይ ያለ በመሆኑ ገና ተደራጅቶ የመብት ጥያቄ የሚጠይቅበት ደረጃ ኣልደረሰም፡፡ ስለዚ በኣገራችን ሊበራሊዝምን መቀስቀስ ደጋፊ የሌለው፣ መሰረት የሌለው ከንቱ ቅዠት ከመሆን ኣያልፍም፡፡

- ምክንያቱ ኣንድን ፓርቲ ሲንቀሳቀስ መብቱን ሊያስከብርለት የቆመ ማሕበራዊ መሰረት መኖር ኣለበት
- ኣሁን በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ሃይሎችም ሁኔታ ስናይ ሊበራል ዴሞክራሲ የሚል መፈክር ቢይዙም፣ የባለሃብቱ መብት ለማስከበር፣ የነፃ ገበያ ህግጋት በተሟላ ሁኔታ ለማስፈፀም ባህሪዩም፣ ብቃቱም፣ ዓቅሙም የላቸውም፡፡

ኣሁን በኢትዮጵያ እጅግ በጣም ትልቅ የገበያ ጉድለት Market Failure ያላት አገር በመሆንዋ ሰፊ ና የተመረጠ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ በመሆኑ ***የልማታዊ መንግስት መስመር ወይም ርእዮት ለኢትዮጵያ የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው***፡፡ በአንፃሩ የሊበራሊዝም መንገድ በድሃዋ ኢትዮጵያ የማይሰራ፣ የቀጨጨ፣ ሃይል የሌለው፣ በባለሃብቱ የሚነዳ መንግስት በመፍጠር፣ ለባለሃብቱ መወዳደሪያ ዓቅም ከመፍጠር ይልቅ ወደ ስልጣን ተጠግቶ ከውድድር ውጭ ሃብት እንዲያካብት የሚያደርግ፣ ህብረተሰቡ በመሰረተ ልማት ዕጦት የሚሰቃይበት፣ ***በባለሃብቱ በጎ ፈቃድ እንዲሟላለት የሚጠብቅ ጠባቂ ህብረተሰብ የሚፈጥር የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ወይም ደግሞ የጥፋት መንገድ ነው፡፡***

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የአማራጭ ጉዳይ፣ የአንድ ፓርቲ የመምረጥና ያለመምረጥ ጉዳይ ሳይሆን ***የህልውና ጉዳይ፣ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የማስጠበቅና ያለማስጠበቅ ጉዳይ፣ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ዕድገት የማስመዝገብና ያለማስመዝገብ ጉዳይ ነው፡፡*** ይህም የፕሮፖጋንዳ ትፍርፍ ለማግኘት የሚነገር ሳይሆን በተግባር ባለፉት 13 ዓመታት በተከታታይ የተገኘውን ድል ማየቱ በቂ ነው፡፡ ለዚህም ነው ባለፉት 25 የዴሞክራሲና የልማት ዓመታት ጊዜ ውስጥ በተካሄዱት 5 ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ነፃ የህዝብ ምርጫ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተቀባይነቱ እያደገ፣ በዚህ መስመር የተመዘገበው ልማት በያንዳንዱ ቤት መግባት ሲጀምር፣ የህዝቡ የንሮ ደረጃ መቀየር ሲጀምር እነሆ በ5ኛው አገራዊ የህዝብ ነፃ ምርጫ ለመጀመሪያ ጊዜ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በተወዳደረባቸው ቦታዎች ሁሉ አሸናፊ ሆኖ ወጣ፡፡

***ስለዚ አብዮታዊ ዴሞክራሲ በመሰረተ ሓሳብም፣ በተግባርም፣ በህዝቡ ተቀባይነት በማግኘትም ወደር የሌለው ኢትዮጵያዊ ርእዮት መሆኑ በተግባር ያስመሰከረ ለኛ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም እንደኛ የመሰሉ አገራት በአጭር ጊዜ ከድህነት አውጥቶ በፈጣን ዕድገት ጎዳና የሚያስገባ የባለቤትነት መብት ልንጠይቅለት የሚገባን ውጤታማ ኢትዮጵያዊ ርዕዮታችን ነው፡፡***

## 4 በአማራጮቹ በመንግስታዊ አወቃቀር ያለው አንድነትና ልዩነት

በአንድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የመንግስት አወቃቀር 3 የመንግስት አካላት ይኖሩታል እነሱም ሕግ አውጪ፣ ሕግ ፈፃሚ እና ሕግ ተርጓሚ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በአገራችን ያለውም እነዚህን የሚያሟላ ነው፡፡ የሊበራል ዴሞክራሲ ተከታዮችም የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተከታዮችም 3ቱ የመንግስት ኣካላት መኖራቸው ይስሚሚሉ፣ ያቋቁማሉ፡፡ 3ቱም የመንግስት ኣካላት ነፃነታቸው ጠብቀው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው፣ ኣንዱን ሌላኛውን ተፅእኖ እንዳያደርስ በአወቃቀርም ትዩዩ ሆነው መዋቀር እንዳለባቸው ሁሉም ይስማማሉ፡፡ በዚህ መሰረት

1. ሕግ ኣውጪው በነፃ ምርጫ በሚመረጥ ፓርላማ እንደሆነ፣

2. ሕግ ፈፃሚው በነፃ ምርጫ ባሸነፈ ፓርቲ የሚዋቀር መንግስት ወይም በጥምር የሚዋቀረው መንግስት ስም የሚቋቋም ካቢኔ ወይም የመንግስት ሚኒስትሮች ምክርበትና በተዋረድ የተቋቋመ የመንግስት ኣካል እንደሆነ፣
3. የዳኝነቱ ስርዓትም ከሁሉም የመንግስት ኣካላት ነፃ በሆነ መንገድ መዋቀር እንዳለበትና ነፃ ሆኖ የዳኝነት ስርዓቱ መፈፀም እንዳለበት ነው፡፡

እዚህ ላይ በሁለቱም ርእዮቶች ጥቃቅን ልዩነት ቢኖሩም መሰረታዊ ልዩነት የለም፡፡ ነገርግን እነዚህ ርእዮቶች ከሚለያዩባቸው መሰረታዊ ልዩነቶች በህግ ተርጓሚው አካል አወቃቀር ላይ ነው፡፡ የእዚህ ላይ መሰረታዊ ልዩነቶች ያሉት እስኪ እንየው፡፡

## 4.1 የሊበራል ዴሞክራሲ ተከታዮች

ሊበራል ዴሞክራሲ መነሻውና መድረሻው የግል መብት ያለምንም መሸራረፍ መከበር ኣለበት ከሚል መርህ በመነሳት የሚወጡ ህጎችም ከዚህ መርህ አንፃር እንዲተረጎሙ፣ ከማንኛውም ፖለቲካ ውጭ በባለሙያዎች መተርጎም ኣለበት፡፡ ስለዚ የህግ ተርጓሚው የመንግስት አካል ከሕግ ባለሙያዎች በተውጣጣ መዋቀር አለበት ሲል፤

## 4.2 የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ተከታዮች

የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መነሻውና መድረሻው የህዝቡን የግልና የቡዱን መብት ያለምንም መሸራረፍ በእኩል መከበር ኣለበት ከሚል መርህ በመነሳት የሚወጡ ህጎችም ከዚህ መርህ አንፃር እንዲተረጎሙ፣ ከብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በነፃ ምርጫ ከተመረጡ ምክርቤቶች በሚወከሉ ኣባላት በተዋቀረ ኣካል መተርጎም ኣለበት፡፡ ይህ ኣካል የቡድን ወይም የብሄር ብሄረሰቦች መብቶች በማይጎዳ መልክ የሚተረጉምና የህዝቡን ፍላጎት በተማላ መልኩ የማረጋገጥ ብቃቱ ከባለሙያዎች የበለጠ ይሆናል፡፡ እዙህ ላይ የሚዋቀረው ህግ ተርጓሚው የፌደረሽን ምክርቤት ባለሙያዎች እንዲ ደገፍ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲኖሩት ተደርጎ የሚዋቀር ሲሆን የማማከር ስራ ይሰራል፡፡ የመጨረሻው ውሳኔ የሚሰጠው ግን ይህ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ውክልና ያለውን የፌደረሽን ምክርቤት ይሆናል፡፡

ጀነራሉ የሚሉት ግን ፓርላማው እና በምርጫ ያሸነፈው ፓርቲ መለያየት አለበት አለበለዚያ ነፃነት አይኖርም፡፡ ይህ ኬት እንዳመጡት ባይገባኝም ግን ደግሞ የራሴን አስተያየት ልስጥ፡፡

***አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወደ ምርጫ ሲገባ ህዝቡ እንዲመርጠው ያለውን ፖሊሲና ስትራቴጂ በማቅረብ፣ ከተመረጠ በመንግስትነት ዘመኑ የሚፈፅማቸው የልማትና የዴሞክራሲ ዕቅዶቹ***

*ያቀርባል፡፡ መንግስትነት የተቆጣጠረ አካል ለህዝብ ቃል የገባውን ነገር መፈፀም የሚችለው በህገመንግስቱ መሰረት በሚያቋቁማቸው 3ቱ የመንግስት አካላት ነው፡፡ መንግስትነት የያዘ ፖለቲካ ድርጅት ለህዝብ የገባውን ቃል ለመፈፀም ከህገመንግስቱ ሳያፈነግጥ ይሆነኛል ያለውን ህግ ወደ ፓርላማ አቅርቦ ሊያፀድቅ ከሆነ ፓርላማውና መንግስት እንዲሁም ፓርቲው መናበብ አለበት፡፡ አለበለዚያ አገር ሊመራ አይችልም፡፡* ለምሳሌ እንደ ጀነራሉ ኣባባል ኢህአዴግ መንግስትነት ተቆጣጥሮ ባለበት ጊዜ ፓርላማው ከኢህአዴግ አባላት ውጭ ከሆኑ ኢህአዴግ የሚያቀርባቸው ሁሉም ውድቅ ያደርጉታል፡፡ ስርዓት የሚባል ነገር የለም፡፡ ስለዚ አሸናፊው ፓርቲ ነፃ መሆን የለበትም የሚባለው ትክክል ኣይደለም፡፡ ምክንያቱ የተረጋጋ የመንግስት ስርዓት የሚያመጣ ሳይሆን *የተመሰቃቀለ፣ መረጋጋት የሌለበት ኣንዱን የመንግስት ኣካል ለውድቀቱ ሌላኛውን የመንግስት ኣካል በመወቃቀስ የሚያሳልፍ፣ 3ቱም የመንግስት ኣካላት ለልማት እንቅፋት የሚሆንበት ነው የሚፈጠረው፡፡*

*በአጠቃላይ ሌ/ጀነራል በአገራችን እየታየ ያለው ችግር የስርዓት ችግር እንደሆነ ለማሳየት የመከሩትን የመንግስት ጣልቃ ገብነትና የህግ አውጪውና ሕግ ፈፃሚው የአንድ ፓርቲ መሆኑ ገልፀዋል፡፡ ግን እላይ ለማየት እንደሞከርነው የመንግስት ጣልቃ ገብነት መኖር ልማቱን ኣፋጠነው እንጂ ችግር አልወለደም፣ ህግ አውጪውና ሕግ ፈፃሚው ከአንድ የፖለቲካ ሪእዮተ ዓለም የሚቀዱ መሆናቸው ኢህአዴግ ለህዝብ የገባውን ቃል በተሟላ መንገድና በሙሉ መግባባት እንዲፈፀም ያደረገ እንጂ ጀነራሉ እንዳሉት ችግር ውስጥ ያስገባን ኣይደለም፡፡ ስለዚ የስርዓት (Systemic) ችግር ነው የሚለው መሰረተቢስ ድምዳሜ ነው፡፡*

## 5 አሁን በአገራችን እየታየ ያለው ችግር ምንድን ነው?

አሁን በአገራችን ላይ እየታየ ያለው ችግር ምንነትና መንስኤ ለማወቅ መጀመሪያ አገራችን ኬት ተነስታ እዚህ ደረሰች የሚለው ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ሁላችንም እንደምናውቀውና የታሪክ አዋራዎች እንደሚያመላክቱት አገራችን ኢትዮጵያ የ3ሺ የስልጣኔና የዕድገት ታሪክ እንደነበራት ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ የማያቧራ የእርስ በርስ ጦርነቶች እንደተካሄዱባት በስተመጨረሻ የዓለማችን የመጨረሻዋ ድሃ አገር ለመባል እንደደረሰች ግልፅ ነው፡፡ በተለይ ባለፉት 100 ዓመታት የነፍጠኛው/ትምክህት ስርዓት ባደረሰው ከፍተኛ ጭቆናና ብዝበዛ በስተመጨረሻ በአንድ በኩል የትምክህቱ አመለካከት ጫፍ የደረሰበት በሌላ በኩል የትምክህት ስርዓት አስከፊ ጭቆና የወለደው ጠባብነት ኣስተሳሰብ ጫፍ ደርሶ አገራችን

በብተናና ዕልቂት አፋፍ ላይ ደርሳ ነበር፡፡ ኢህአዴግ ባይደርስላት ኑሮ አሁን ምናልባት አገራችን ልዩነቶችን መቻቻል አቅቷት እንደነ ሶማሊያ፣ ሶሪያና ሊብያ ትሆን ነበር፡፡

ደርግ እንደተደመሰሰ ዋናው ጉዳይ ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን፣ ልዩነቶች ዕውቅና በመስጠት ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፣ የተገደቡ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ ማድረግ፣ በሂደትም የሁሉም የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተሳትፎ ያረፈበት ህገመንግስት በማፅደቅ ህገመንግስታዊ ስርዓት መገንባት የሚል እርምጃ ተወስዶ በመበታተን አፋፍ ላይ ደርሳ የነበረችውን አገራችን ወደ መቻቻል፣ መከባበር፣ ልዩነቶችን ማጥበብና ወደ ዴሞክራሲያዊ አንድነት አቅጣጫ እንድታመራ በቃች፡፡

በዚህ ጊዜ ህዝቡም የሚጠቅመውና የማይጠቅመው እየለየ፣ ፀረ ህዝቦችም ከህዝቡ እየተነጠሉ ሲሄዱ፤ ይህንን መቋቋም ያቃታቸው እንደነ ኦነግና ኦብነግ ወደ ሽብር ተግባር ገብተው ህዝብን ማሰቃየት ስራችን ብለው መያዛቸው የቅርቡ ዓመታት ትውስታ ነው፡፡ ለምሳሌ የበደኖ ዕልቂትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ በዚህ የ25 ዓመት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ከትጥቅ ትግሉ ባልተናነሰ ከፍተኛ መስዋእትነት በመክፈል 5 ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ነፃ ምርጫ በማካሄድ አሁን እዚህ ደረጃ ደርሰናል፡፡ በነዚህ 5 ምርጫዎች ህዝቡ የሚጠቅመውና የማይጠቅመው በመለየት የራሱን ነፃ ምርጫ በማካሄድ ከጊዜ ወደ ጊዜ የጠባቦችና የትምክህት ሃይሎች እየለያቸውና የምርጫ ካርዱን እየነፈጋቸው እነሆ በ5ኛው የህዝብ ምርጫ በባዶ ሸኛቸው፡፡ ይሁንና አሁንም መልካቸው እየቀያየሩ አፍራሽ ተግባራቸውን አልተዉትም፡፡

በልማቱ በኩልም ባለፉት 25 ዓመታት አገራችን ከየኋልዮሽ ጉዞ (ከነጋቲቭ ዕድገት) ወጥታ ወደ ፖዚቲቭ ዕድገት የደረሰች በተለይ ከተሃድሶ ቦኋላ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ዕድገት በማምጣት ከዓለማችን የምትጠቀስ አገር ለመሆን በቅታለች፡፡ ***ለዚህ ማሳያ የሚሆነው ዘንድሮ የገጠመንን የድርቅ አደጋ ከ1977 ዓ.ም. የከፋ ድርቅ እያለ መንግስት ያለዕርዳታ መቋቋም መቻሉ ባለፉት 25 ዓመታት ያስመዘገብነው ዕድገት ትምክህተኞችና ጠባቦች እንደሚሉት በከተሞች ብቻ የሚታይ የህንፃና የቁጥር ድርደራ ሳይሆን በተግባር የታየ በያንዳንዱ ቤት የገባ ተጨባጭ ዕድገት ነው፡፡*** አሁን እየገነባን ያለነው ስርዓት የመንግስት ሰፊ ጣልቃ ገብነት ያለው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት እንደመሆኑ መጠን እንደማንኛውም ይህን ስርዓት የሚከተል አገር የሚገጥመውም ችግር እኛንም እንደሚገጥመን በማወቅ አስቀድመን እየተከላከልንና እየሰራን እንገኛለን፡፡ በተሃድሶ የመስመር ማጥራት ጊዜ የለየነው ነገር ቢኖር ይህ ነው፡፡ እሱም የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር፡፡

## 5.1 ኪራይ ሰብሳቢነት የስርዓታችን ዓደጋ

በተሃድሶው ላይ እንደምናስታውሰው የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ በሁለት ከመሰንጠቁ በፊት ውይይት ሲጀመር ***አሁን በግል ስራ ላይ የሚገኙ ሁለቱ ጀነራሎች ማለትም (ሌ/ጀ ፃድቃን ገ/ትንሳኤና ሜ/ጀ አበበ ተ/ኋይማኖት) ተጋብዘው ፅሁፉ ተሰጥቷቸው አንብበው እንዲመጡና ገንቢ ሃሳብ እንዲሰጡ ዕድል ተሰጥቷቸው ነበር፡፡*** በዛን ጊዜ ከምንገነባው የነፃ ገበያ ስርዓት አንፃር እንዲሁም ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት ዋናው ችግራችን ምንድነው የሚለው ጥያቄ ተነስቶ የተጧጧፈ ውይይት ሲደረግ ክቡር መሪያችን ኣቶ መለስ ዜናዊ ዋናው ችግራችን ሙስናና ፀረ ዴሞክራሲ ናቸው ሲል አንጃው ደግሞ ለኢምፔሪያሊዝም ተምበርካኪነትና ሉኣላዊነትን ያለመጠበቅ ነው የሚል ተነስቶ ክርክር ሲደረግ ***ሁለቱ ጀነራሎች ችግራችን ሙስናና ፀረ ዴሞክራሲ ብለን ከወጣን ድርጅቱ ይበታተናል፣ ከደሙ ንፁህ ነን ብሎው ሲያፈገፍጉ*** የለውጡና የተሃድሶው ሃይል አሸናፊ ሆኖ በመውጣቱ ይኸው በለውጥና በህዳሴ ጎዳና እንገኛለን፡፡

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ነበር የስርዓታችን ዋናው አደጋ የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ ነው መገለጫውም አለአግባብ የመጠቀም አስተሳሰብና ተግባር ነው፡፡ አገራችን የምታራምደው የነፃ ገበያ ስርዓት ባህሪ ጥራት ያለው ምርት በማምረት በሚፈለገው ቦታና ጊዜ በተሻለ ዋጋ በማቅረብ ተወዳዳሪ መሆን ነው፡፡ የተዋጣለት የነፃ ገበያ ስርዓት እንዲኖር ከተፈለገ ያሉትን የገበያ ጉድለቶች ተሟልተው መቅረብ አለበት፡፡ ***ባለሃብታችን ተወዳድሮ የአገር ውስጥም ውጭም ገበያ አሸናፊ ሆኖ እንዲገኝ እላይ ለመጥቀስ የተሞከሩት የተሟላ የመሰረተ ልማት አቅርቦት፣ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኋይል አቅርቦት፣ የተሟላ የትራንስፖርትና ኮሚኒዩኬሽን አቅርቦት፣ የተሟላ የፋይናንስ አቅርቦት፣ ተወዳዳሪ ቴክኖሎጂና መሳሪያዎች፣ ብቁ የቢዝነስ አመራርና መዋቅር፣ ወዘተ ተሟልተው ሲገኙ ነው፡፡ እንደኛ ባሉ ድሃ አገሮች እነዚህ ነገሮች ተሟልተው ኣይገኙም፡፡*** አሁን ባለንበት ዘመነ ግሎባላይዜሽን ውድድሩ እላይ የተዘረዘሩትን ከተሟላላቸው አገሮች ጋር ነው፡፡ ውድድሩ የተሟላ ትጥቅ ካለውና ምንም ትጥቅ ከሌለው የሚደረግ በመሆኑ ውድድሩ ፍትሃዊነት ይጎድለዋል፡፡ ግን ደግሞ ፍትሃዊነት ታግሎ ማረጋገጥ እንደሚቻል የነኮርያና ታይዋን መንገድ አረጋግጦልናል፡፡

ኢትዮጵያ የድሆች ድሃ በመሆንዋ እላይ የተዘረዘሩ አቅርቦት በተሟላ መልኩ የላትም ስለዚ የተሟላ የነፃ ገበያ ውድድር ለማድረግ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ለዚህ ነው አሁን ባለንበት ሁኔታ በልማታዊ መንገድ ሳይሆን በኪራይ ሰብሳቢ መንገድ በመሄድ የተመቸ ነው የምንለው፡፡ ***ምክንያቱ እነዛ የመወዳደሪያ ትጥቆች በተሟላ ሁሌታ ስለሌሉ፣ ጥራት ያለው***

*ምርት በማምረት በነፃ ገበያ ተወዳድሮ ማሸነፍ አስቸጋሪ ስለሚያደርገው አጭሩ የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ማለትም ከመንግስት ባለስልጣናት በመመሳጠር ምርትህ ወይም አገልግሎትህ የማይገባው ዋጋ እንዲያገኝ በማድረግ የሚገኘው ትርፍ በባለሃብቱና በባለስልጣኑ ክፍፍል ሲደረግ ህዝቡ ጥራቱ የተጓደለ ምርት ወይም አገልግሎት በማግኘት ሲሰቃይና የማይገባው ክፍያ ሲከፍል ይኖራል ማለት ነው፡፡* ስለዚ በዚህ አኳኋን መወዳደር የሚባል ነገር አይመጣም፣ ዕድገት የሚባል ነገር አይታይም፡፡ በነፃ ገበያ ስም አገሪቷ ጥቂት ባለሃብት ከጥቂት ባለስልጣን ተመሳጥሮ ይቆጣጠሯትና ህዝቡ በድህነት እንዲኖር ይፈረድበታል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ነው በእንደኛ ዓይነቱ ድሃ አገሮች በነፃ ገባያ መርህ መርህ ውስጥ ሲራመዱ በጣም ትልቅ የኪራይ ሰብሳቢነት አደጋ ከፊታቸው ተደቅኖ እንዳይንቀሳቀሱ ያደርጋል የሚባለው፡፡ *ለዚህ ነው በአብዮታዊ ዴሞክራሲ፣ ለልማት በምናደርገው ጉዞ ኪራይ ሰብሳቢነት ዋነኛ የስርዓታችን ዓደጋ ነው የሚለው፡፡* *እዚህ ላይ በስልጣን ላይ ያለው አካል ከሚገባው በላይ ሃብት ስለሚቀርብለት ይጎመጃል፣ ባለሃብቱም ተወዳድሮ ለማሸነፍ በጣም ትልቅ ጥረትና ድካም የሚጠይቅ ሆኖ ከባለስልጣን ተመሳጥሮ መኖር ደግሞ አጭርና ቀላል ሆኖ ስለሚያገኘው የሚመርጠው አጭሩና ቀላሉ የመክበር መንገድ ነው፡፡* ለዚህ ነው የአገራችን ሁኔታ ከልማታዊ ይልቅ ለኪራይ ሰብሳቢነት የተመቸ ነው የሚባለው፡፡

*አሁን ባለንበት ግሎባላይዜሽን አገራችን በነፃ ገበያ*

- ዕድገት እያስመዘገበ መቀጠል የሚችለው፣
- አስጎምጂ ስጦታዎችና ጥያቄዎች ትቶ የህዝቡን ከድህነት መውጣት ጥያቄ ማስቀደም የሚችለው፣
- አስጎምጂ ስጦታዎችና ጥያቄዎችን የሚያቀርብ ኪራይ ሰብሳቢ ባለሃብት ወደ ትክክለኛ ልማታዊ መስመር ማስገባት የሚችለው፣
- ህዝቡ ከድህነት ለማውጣት ህዝቡን በልማታዊ ሰራዊት አደራጅቶ ወደ ልማት ማዝመት የሚችለው፣
- ያለውን ሃብት አሟጦ በልማት ማዋል የሚችለው

*ህዝቡን ከድህነትና አስከፊ ጭቆና ለማላቀቅ ከባድ መስዋዕትነት የከፈለውና አሁንም በመከፈል ላይ ያለው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ሓይል ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ነው አብዮታዊ ዴሞክራሲ ለኢትዮጵያ የፓርቲ ምርጫ ሳይሆን አገር እንደ አገር ቆማ ለመሄድ ወሳኝ መስመር ነው የምንለው፡፡*

አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር እንከን የለሽ መስመር ቢሆንም ምንም አደጋ አያጋጥመውም ማለት አይቻልም ምክንያቱም ይህ መስመር የሚመሩት መላዕክት ሳይሆኑ ሰዎች በመሆናቸው የኪራይ ሰብሳቢነት ዓደጋ ሊያንዣብባቸው ይችላል፡፡ ለዚህ ነው ***ኪራይ ሰብሳቢነት በነፃ ገበያ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዋናው አደጋ ነው የምንለው፡፡***

አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን ዋናው የስርዓታችን አደጋ ኪራይ ሰብሳቢነት መሆኑ ብቻ ያሳየን ሳይሆን፣ የመታገያ ኣቅጣጫዎችም በመለየት፣ በአጭርጊዜና በረጅም ጊዜ መታገያ መዋቅሮችና አደረጃጀቶችን በመፍጠር፣ የህግ ድጋፍ እንዲያገኙ መታገያ ኣዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በማውጣት፣ የዕለት ተዕለት የመታገያ ስልቶችን በመንደፍ ስንታገላቸው ቆይተናል፡፡

***የአገራችን ሁኔታ ሲታይ የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነት ያረጋገጠበት ከልማታዊነት ይልቅ ለኪራይ ሰብሳቢነት የሚመች እንደሆነና፣ በፍጥነት ድህነት በማጥፋት የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ከተፈለገ፣ ያለውን የኪራይ ሰብሳቢነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ በልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ መተካት እንዳለብን በመገንዘብ፣ የልማትና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ዙርያ ያሉን ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በሙሉ ሲነደፉ የኪራ ሰብሳቢነት የፖለቲካል ኢኮኖሚ መድፈቅ ግምትውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡***

በዚህ መሰረት ባለፉት 13 ዓመታት ኪራይ ሰብሳቢነትን በመታገል ያስመዘገብነው ድል ሲታይ ኣሁን የገጠሩ ሁኔታ የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነቱ ያረጋገጠበት ደረጃ የተደረሰ ሲሆን በከተማ ላይ ግን ገና የኪራይ ሰብሳቢነት የፖለቲካል ኢኮኖሚ የበላይነቱ እንዳረጋገጠ ይገኛል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ባለፉት 13 ዓመታት በሰራነው ስራ አበረታች ውጤት የተገኘበትና የተከተልነው የትግል ስልት ውጤታማነትን ነው፡፡

***አሁን ባለንበት ህገመንግስታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያችን ያለው ፖለቲካ በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ፖለቲካ ነው፡፡ እነሱም፡-***

1. ***የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ*** እና
2. ***የልማታዊ ዴሞክራሲ መንገድ*** ናቸው

***በአገራችን ከ60 እስከ 75 የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች ቢኖሩም ሁሉም ከነዚህ ሁለት ክፍሎች ውጭ አንድም የለም፡፡ ኪራይ ሰብሳቢነት ከስልጣን ውጭ መንቀሳቀስ ስለሚቸገር ስልጣን የማግኘት ትግል የሞት ሽረት ትግል ያደርጋል፡፡ ስለዚ የጀመርነውን***

*የኪራይ ሰብሳቢነት ትግል ፍሬ በማፍራት ላይ በመሆኑ አጠናክሮ መቀጠል እንጂ ሌላ አማራጭ ሁሉ የውድቀትና የኪራይ ሰብሳቢነት አማራጭ ነው፡፡*

# 6 የኪራይ ሰብሳቢነት መደበቂያ ዋሻዎች

ኢትዮጵያ የብዙ ብሄር ብሄረሰቦች አገር ከመሆንዋ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ የኣኗኗር ዘይቤ፣ እምነቶች፣ ሃይማኖቶች፣ ወዘተ ያላት አገር ናት፡፡ ከዚህ ልዩነቶችን የሚነሱ የተለያዩ ፍላጎቶችና ልዩነቶችን መኖራቸው የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ እነዚህ ልዩኖቶችና ፍላጎቶችን ኣቻችሎ የመምራት ጉዳይ ኣንገብጋቢ ጉዳይ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን ላለፉት ዘመናይ እነዚህን ልይኖቶች ኣቻችሎና ኣጣጥሞ ከመምራት ይልቅ ኣንዱን ወገን ከሌላው ወገን በማጋጨት ለመፍታት ይሞከር ስለነበር ባለፉት ጥቂት መቶ ኣመታት የጠባብነትና የትምክህተኝነት ኣፍራሽ ኣመለካከቶች በህዝቡ ዘንድ ስር እየሰደዱ በመምጣታቸው፣ ኣሁን ለደረስንበት ድህነትና ኋላ ቀርነት የራሱን ኣስተዋፅኦ ኣድርጓል፡፡

ከረጅም ዓመታት የተበታተነ የህዝቦች ትግል እና ከ17 ዓመት መራራ የተደራጀ የህዝቦች ትግል ቦኋላ በህዝቦች ጫንቃ ተጭኖ ለዘመናይ ይኖር የነበረውን *የትምክህት ስርዓት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ፣ እንደ ስርዓት ላይመለስ ተንኮታኩቶ ተሰባብረዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህን ስርዓት የረጨው የትምክህት ኣስተሳሰብ መርዝና የዚህ ስርዓት ኣስከፊ ጭቆና የወለደው የጠባብነት መርዝ በህዝቡ ውስጥ ተረጭቶ ገና ብዙ የማፅዳት ስራ የሚፈልግ ጉዳይ ሆኖ ይገኛል፡፡* ትምክህትና ጥበት እንዲሁም የኋይማኖት አክራሪነትና ሽብርተኝነት አራማጅ ኋይሎች ቅንጣት ታክል የህዝብ ወገንተኝነት የሌላቸው፣ በህዝቡ የልማትና የዴሞክራሲ ጥያቄ ውስጥ ተሸጉጠው ስልጣን በመያዝ ለመክበር የሚሯሯጡ ናቸው፡፡ የነዚህ ኪራይ ሰብሳቢ ኋይሎች ዋና መሸሸጊያ ዋሻም ይህ ትምክህት፣ ጥበትና የኋይማኖት አክራሪነት ናቸው፡፡

ይህን ኋላቀርና ኣፍራሽ አመለካከት (ትምክህትና ጥበት እንዲሁም የኋይማኖት አክራሪነትና ሽብርተኝነት) በህዝቡና በጥቂት ኣመራሩ ዘንድ ስር ሰዶ በመቆየቱ ኣሁን የምናደርገው የልማትና የዴሞክራሲ እንቅስቃሴ መልኩን እየቀያየረ ብቅ ጥልቅ እያለ እንቅፋት በመፍጠር ላይ ይገኛል፡፡ *አሁን ካለው የአገራችን ሁኔታ ትምክህትና ጥበትን ዘርዘር አድርገን እንይ፡፡*

## 6.1 ትምክህተኝነት

ትምክህተኝነት ማለት የብሄር ህልውናና ስያሜ እንዳለ ቢክድም በኣንድነት ስም የኣንድን ብሄር ቋንቋ፣ ባህል፣ የኣኗኗር ዘይቤ ብቻ ዕውቅና በመስጠት የሌሎችን ብሄር ብሄረሰቦች

ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ ባደባባይ በመካድ ዕውቅና እንዳያገኙ፣ በአንፃሩ የአገራችን ብሄር ብሄረሰቦች የራሳቸውን ማንነት፣ ቋንቋ፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤ በተለያዩ ጫናዎች እንዲተዉት በማድረግ በአንድነት ስም ዕውቅና ያገኘውን ብሄር ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ዘይቤ ብቸኛ የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ስያሜ ተሰጥቶት እንዲከተሉት የሚያስገድድ፤ ከዚህ ውጭ የሚንቀሳቀሱና የሚከተሉ ደግሞ እንዲሸማቀቁና ከዛ አልፎ መንግስታዊ አገልግሎቶች እንዳያገኙ የሚያደርግ ኋላ ቀር አስተሳሰብ ነው፡፡

***የዚህ አፍራሽ አስተሳሰብ ፕሮፖጋንዳ*** የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት ያለ ገደብ ከተከበረ የአገር አንድነትን አደጋ ላይ ይወድቃል፤ ***ስለዚ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት ያለገደብ መከበር የለበትም፣ በብሄር ብሄረሰቦች ስም መደራጀትም የለበትም፣ ብሄር ብሄረሰቦች በባህላቸው፣ በማንነታቸውና በቋንቋቸው እንዲደራጁ፣ እንዲከለሉ ከተደረገ ለኢትዮጵያ አንድነት አደጋ ይሆናል ስለዚ በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ እንዲኮሩ አስተዳደራዊ አከላለል ወይም አደረጃጀት በጂኦግራፊያዊ፣ በወንዞችና፣ ሸለቆዎች፣ ሸንተረሮችና ተራሮች መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡*** ለባህል፣ ለቋንቋና ለብሄር ማንነት ማሳደግና ማበልፀግ ዕድል መስጠት የለበትም፡፡ በማለት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪም መሰረታዊ የዴሞክራሲ መብቶችን በመገደብ እልም ያለ ፀረ ዴሞክራሲ የሆነ አስተሳሰብ የሚያራምድ ኋላ ቀርና ከዘመኑ የማይሄድ አፍራሽ አስተሳሰብ ነው፡፡

እንግዲህ ይህ ነው ከማንም በላይ ኢትዮጵያን የመበታተንና የማፈራረስ አደጋ ሆኖ ሊመጣ የሚችለው፡፡ እነ ሻዕብያ ሆነ ሌሎች ኪራይ ሰብሳቢ ኀረቤቶች ***"ኢትዮጵያን ማንበርከክ የሚቻለው በውስጥ አለመረጋጋት በመፍጠር እንጂ፣ ዱሮም አሁንም በሃይል ማንበርከክ አይቻልም"*** የሚል ድምዳሜ በመውሰድ የትምክህት ሃይሎችን በማደራጀትና በመደገፍ ወደ ውስጣችን እንዲገቡ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡

የትምክህት ሃይሎችም በጦርነት ወይም በሃይል የማሸነፍ ሆነ የማነቃነቅ አቅም እንደሌላቸው እነሱ ራሳቸው የሚያውቁት ጉዳይ ነው፡፡ ያላቸው ሃይል ለፕሮፖጋንዳና ለሽብር ብቻ የሚያገለግል እንጂ አንድ ሃይልም ማፍረስ የሚችል ብቃቱም ወኔውም የላቸውም፡፡

ቀንደኛ የዚህ አፍራሽ ዓላማቸው መሳሪያ ወይም ቦንብ፣ በህዝቡ ላይ ያለውን የተሳሳቱ አመለካከቶችን ስሜታዊ በሆኑ ነገሮች እንደ ክርቢት በመጫር ህዝቡ በራሱ ስርዓት ላይ እንዲያምፅና ህገመንግስታዊ ስርዓቱ እንዲያፈርስ ማድረግ ብቻ ነው፡፡ ***እዚህ ላይ የሚከተሉትን ዘዴ ውሸትና አሉባልታ በመንዛት ነው፡፡ ይህ ስልት ባለንበት ዘመን በዘመ***

***ኢንፎርሜሽን ብዙ የማያዋጣና የማያዛልቅ ቢሆንም አፍራሽ ዓላማ ያለው ሃይል ግን ለአንድቀንም ቢሆን ተጠቅሞ ግርግር በመፍጠር ስርዓት የለሽ ለመፍጠር ሲጥሩ ይታያሉ፡፡***

ለምሳሌ አሁን በሰሜን ጎንደር የተነሳው ዝርፍያና ብጥብጥም በምናይበት ጊዜ በተመሳሳይ በውሸትና አሉባልታ ህዝብን ለማነሳሳት የተሞከረበት፣ አሁንም አንድን ህዝብ ላይ ታርጌት በማድረግና በጠላትነት በመፈረጅ በትግራይ ተወላጆች ላይ ዝርፍያና የንብረት ማውደም ማቃጠልና ማፍረስ ተግባራት ተስተውሏል፡፡

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ህገመንግስታዊ ስርዓት መሰረት ስልጣን የሚያዘው በነፃ የህዝብ ምርጫ ሆኖ ሳለ፣ እያንዳንዱ ክልል የራሱን ብሄር ተወላጅ ይወክለኛል የሚለውን ግለሰብ ወይም ፓርቲ የሚመርጥበት ሁኔታ እያለ፣ በመሆኑም ለአብነት የ2007 ምርጫ እንኳ ብንወስድ

| ተቁ | ክልል | ለክልል ተወካዮች | ለፌደራል ተወካዮች |
|---|---|---|---|
| | ትግራይ | 125 የክልሉ ተወላጆች | 38 የክልሉ ተወላጆች |
| | አማራ | 294 የክልሉ ተወላጆች | 137 የክልሉ ተወላጆች |
| | ኦሮምያ | 537 የክልሉ ተወላጆች | 178 የክልሉ ተወላጆች |
| | ደቡብ ህዝቦች | 348 የክልሉ ተወላጆች | 122 የክልሉ ተወላጆች |
| | አዲስ አበባ | | 23 የክልሉ ነዋሪዎች |
| | ድሬዳዋና ሃረሪ | | 2 የክልሉ ነዋሪዎች |
| | ጠቅላላ | | 500 |

በተጨባጭ ሁሉንም የሚያውቀው፣ አገራችን በህዝቡች ነፃና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ በተመረጡ ተወካዮች የተዋቀረ የየክልሉ መንግስት ተቋቁሞ የየራሱ ክልል፣ ባህል፣ ቋንቋ በማሳደግ ላይ ያለ ሞሆኑና እነሆ ላለፉት 13 ዓመታት ለዓለም ያስደነቀ ዕድገት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ ***ታዲያ ትምክህተኞች አሁን በምን ስሌት ነው በያንዳንዱ ክልል ህወሓት ወይም የትግራይ ተወላጆች ናቸው የሚመሩህ የሚባለው?***

- ***በፌደራል ደረጃም ቢሆን ካሉት 500 ወንበሮች የትግራይ ወይም የህወሓት ድርሻ 38 ሆኖ ሳለ በምን ስሌት ነው የፌደራሉ የመምራት ሚና በትግራይ ተወላጆች ስር ነው የሚባለው?***
- ***በፌደራል ካሉት 30 የሚኒስተር መስሪያቤቶች ውስጥ በትግራይ ተወላጆች የተያዘው 4 ሆኖ ሳለ እንዴት በምን ስሌት ነው ፌደራል መንግስት በትግራይ ተወላጆች ነው የተጥለቀለቀው የሚባለው?***
- ***ጠቅላይ ሚኒስተሩ፣ የመከላከያ ሚኒስተሩ፣ የፌደራል ፖሊስ ኮሚሽነሩ፣ የሚመሩት ከትግራይ ተወላጅ ውጭ እያሉ ህወሓት ነው የሚባለው በምን ስሌት ነው?***

በቅርቡ በጎንደር በፀረ ህዝቦች የተነሳው ብጥብጥ ምክንያት ለህዝብ ሲሉ የተሰዉት 9 የፌደራል ፖሊሶች የብሄራቸውን ሁኔታ ሲታይ

1. ኮማንደር ሃለፎም አዳነ እንደሻው (ፀለምት - ትግራይ)
2. ሳጂን አለሙ መላኩ እንኳንሆነ (ደባርቅ - ሰሜን ጎንደር)
3. ኮንስታብል ኤቢሳ ኢታና አብዲ (ቄለም ወለጋ)
4. ሳጂን ናስሮ ምሹሮ እስማኤል (ደባርቅ -ሰሜን ጎንደር)
5. ረዳት ኢንስፔክተር አህመድ ሁሴን አህመድ (ስልጤ - ደቡብ ክልል)
6. ምክትል ሳጂን አብዲሳ አለሙ ዳሮምሳ (ም/ሸዋ)
7. ምክትል ሳጂን አትሎግ አሰፋ አበራ (ታች ጋይንት - ደቡብ ጎንደር)
8. ረዳት ኢንስፔክተር አደም አብዱላሂ ማኦ (ሊበን - ሶማሌ ክልል)
9. ምክትል ሳጂን ብርሃኑ ሱሊቶ አበሜ (ሃድያ - ደቡብ ክልል) ነው፡፡

***ታድያ በምን ስሌት ነው የህወሓት ልዩ ሰራዊት ነው የሚባለው?***

በጣም ብዙ ጥያቄዎች ማንሳት ይቻላል ግን የትምክህተኞችን ሴራ ለማጋለጥ ይህ ይበቃል፡፡

ሁሉም የጠራ የማያደናግር ውሸት፣ በዘመነ ኢንፎርሜሽን አንድ ቀን የማይሻገር ውሸት ነው፡፡ በውሸት የሚገነባ ስርዓት ፈፅሞ የለም፡፡ ዓላማው አጥፍቶ መጥፋት፣ በህዝቦች መካከል መቃቃር መፍጠር፣ የህዝብና የመንግስት ንብረት ማውደም፣ በአጠቃላይ የጥፋት ዓላማ ያነገበ ቅንጣት ታክል እውነታ የሌለው ነው፡፡

እዚህ መታወቅ ያለበት ***በአንድ ህዝብ ላይ ጥላቻ ያለው አመለካከት በማንም ህዝብ ላይ ፍቅር የለውም፡፡*** ትምክህተኞች የነሱ ኣመለካከት ያልተጋራ ህዝብ ጠላታቸው በመሆኑ እንደ ልማዳቸው ህወሓት ወይም ትግሬ የሚል ታርጋ በመለጠፍ ለማደናገር ይሞክራሉ፡፡

**የጎንደር ህዝብ የአማራ ህዝብ በምርጫ 2007 ብአዴን ያቀረበለትን ዕጩ ተመራጮች በደንብ ገምግሞ ኣውጥቶ ኣውርዶ በአስር ጣቶቹ ፈርሞ የመረጣቸው ወገኖቹ፣ የቋቋመው መንግስቱ፣** የትምክህት ሃይሎች አሁን ተነሳስተው ***የመረጥካቸው፣ የአማራ ተወላጆች ሳይሆኑ የህወሓት ትግሬዎች ናቸው፣*** ሲሉ ነበር ***"ጉድ በል ጎንደር ትምክህተኞች መጡ እነ መልአኩ ተፈራ መጡ ልጆችህን ሊያሳዩህ"*** ብሎ ህዝቡ የተረተባቸው፡፡

ትምክህተኞች የህዝብ ንቀት ስላላቸው፣ ህዝብን የማይገባው ዶንቆሮ ነው ብለው ስለሚያስቡ የገዛ ልጁን ልጅህ ኣይደለም፣ የገዛ መንግስቱ መንግስትህ ኣይደለም፣ የገዛ ህገመንግስቱ ህገ ኣራዊት ነው፣ የገዛ ብሄሩ ብሄርህ አይደለም በማለት **አንድቀን የማይሻገር ውሸት በመዋሸት**

ለማነሳሳት መመኮራቸው ቂልነትና ገና ከ19ኛው ክፍለዘመን ያልተላቀቁ መሆናቸውን ያሳያል፡፡

- ጎንደርን ጨምሮ በመላ ኢትዮጵያ ማንም ኢትዮጵያዊ ይቅር ሌላ ከባዕድ አገር የመጣም ሳይቀር ኢንቨስት እንዲያደርግ በስንት ዲፕሎማሲያዊ ትግል አገራችን መጥታቹ ኢንቨስት አድርጉ ልማታችን አፋጥኑ እያልን ስንማፀን ትምክህተኞች ግን የትግራዋይ ኢትዮጵያዊ ሃብትና ኢንቨስትመንት ያቃጥላሉ፣
- የኢትዮጵያ ህዝብ ልማቱ አፋጥኑት፣ የአገልግሎት አሰጣታቹ አስተካክሉት፣ የትራንስፖርት ችግሮቻችን ፍቱልን፣ ያሉትን የመልካም አስተዳደር ችግሮችን እንዲፈቱ በሚጠይቅበት ወቅት፣ ትምክህተኞች ግን ለህዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ የሰላም አውቶብሶችን ያቃጥላሉ፤

ለዚህ ነው ትምክህተኞች ፀረ ህዝቦች፣ ፀረ የአማራ ህዝብ፣ ፀረ የጎንደር ህዝብ ናቸው የምንለው፡፡ ታዲያ ይህ የፀረ ህዝቦች ተግባር እንጂ የህዝብ ንብረት የሚያወድም፣ የግልም የመንግስትም ኢንቨስትመንት የሚያቃጥል አካል ቅንጣት የህዝብ ወገንተኝነት የለውም፡፡ ስለዚ በህዝቡ ላይ ያለውን ኋላቀር ኣመለካከት በሰለጠነና ዴሞክራሲያዊ፣ ነፃና ግልፅ ኣሰራር መርህ በመከተል መቅረፍ ዋነኛ ተግባራችን መሆን ኣለበት፡፡

ይህን ኣፍራሽ ኣስተሳሰብ በተግባር የከሰረ እንደሆነ ማንም የሚያውቀውና የኢትዮጵያ ህዝብ ከኣንድ ክፍለዘመን በላይ ሲታገለው ከቆየ በኋላ በ17 ዓመት መራራ የትጥቅ ትግል ስርዓቱ እንደ ስርዓት ሊፈራርስ በቅቷል፡፡ የትምክህት ስርዓት የፈራረሰ ቢሆንም ኣስተሳሰቡ ግን ገና በልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ኣስተሳሰብ ሙሉ በሙሉ ኣልተተካም፡፡ በመሆኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀያየር ለልማታችን እንቅፋት ለመሆን እየሞከረ ው፡፡

## 6.2 ጠባብነት

ጠባብነት ማለት የብሄር ብሄረሰቦችን ዴሞክራሲያዊ መብቶች የማስከበር ጥያቄ ተገን በማድረግ የሌሎች ብሄረሰብ መብቶችን በመርገጥ የራሱን ድብቅ ዓላማ ለማርካት የሚንቀሳቀስ ኣፍራሽ ሃይል ነው፡፡ ጠባብነት ኣመለካከት ባለፈው ስርዓት እንደኔ የተበደለ፣ የተረገጠ፣ የተጮቆነ የለም፣ ስለዚ ኣሁን ይህንን ለማካካስ ስልጣኑ ለኔ መሰጠት ኣለበት ካልሆነ እኔ ለብቻየ ተገንጥየ ስልጣኑ ይገቼ የፈለኩት ኣደርጋሎ፤ እኔ ነፃነቴ ማግኘት ኣለብኝ እንጂ ለዘመናት ከጮቆኑኝ ኋይሎች ኣብሬ መኖር ኣልፈልግም፤ እከሌ ብሄር ወይም ደግሞ ሌሎች ብሄሮች ሁሉም በራሴ የተፈጥሮ ሃብት እየመዘበሩ ነው የሚኖሩት ስለዚ እኔ ነፃነቴ

***በማረጋገጥ የተፈጥሮ ሃብቱን ለብቻየ እጠቀማለሁ፣ የኔ የለማ መሬት፣ ወርቅ፣ ነዳጅና ማዕድናት ስላለኝ ለብቻየ ተገንጥየ የተፈጥሮ ሃብትን በመሸጥ መክበር ይቻላል፣ እኔ ድሮ ስለተበደልኩ ኣሁን በተራየ በሌላው ብሄር የበላይነት ማረጋገጥ ኣለብኝ፣ የኔ ህዝብ ከሁሉም በብዛት ስለሚበልጥ የኔ ቋንቋ ባህል በሌላው ላይ መጫን ኣለበት፣ ለእከሌ ብሄር ይህ እየተደረገ ለኔ ኣልተደረገልኝም፣ ይህም ብቻ ሳይሆን በአንድ ብሄር ውስጥ በጂኦግራፊ፣ በዞንና በወረዳ በመከፋፈል ለኔ ሳይደረግ ለሌላ እየተደረገ ነው፣ ወረዳ ወይም ዞን ባለመሆናችን እየተበደልን ነው፣ የራሳችን ክልል ማቋቋም አለብን ወዘተ በማለት ቅሬታዎች እንዲነሱ የሚያደርግ አፍራሽ አመለካከት ነው፡፡***

በአጠቃላይ ጠባብነት የሌሎችን ብሄር ብሄረሰብ መብት ወደጎን በመተው የራስን ብሄር ሽፋን በማድረግ ድብቅ ግላዊ የስልጣን ጥም ለማርካት የብሄሩን መብት ብቻ በማራገብ ከተቻለ የብሄሩን የበላይነት በማረጋገጥ የሌሎችን መብት መርገጥ ካልተቻለ የራሱን ኢምፓየር በመፍጠር የጌቶቹን ኣገዛእ በብሄሩ ማስፈን ነው፡፡ ስለዚ የጠባብነት ኣመለካከት የአንድን ብሄር ህልውና ብቻ የሚያራግብ፣ የሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን ልዩ ባህሪና ፍላጎት የሚክድ በመሆኑ ፀረ ዴሞክራሲያዊና ፀረ ህዝብ ኣፍራሽ ኋይል ነው፡፡ ጠባቦች እንደ ትምክህተኞች የሚከተሉት የትግል ስልት ውሸትና ኣሉባልታ ነው፡፡

ለምሳሌ ***በቅርቡ በኦሮሚያ የአዲስ አበባና የአዲስ አበባ ዙርያ የኦሮሚያ ዞን የልማት ማስተር ፕላን ምክንያት በማድረግ የደረሰው ብጥብጥና ውድመት በምናይበት ጊዜ ያልተባለ ተባለ፣ ያልተደረገ ተደረገ፣ ያልታሰበ ታሰበ በማለት በውሸት ህዝቡን ለማነሳሳት የተሞከረ፣ አንድን ህዝብ በጠላትነት በመፈረጅ በህዝቦች ላይ መቃቃር ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡***

**ጠባቦችና እንደ ትምክህተኞች ድብቅ ግላዊ የስልጣን ጥማትን ለማሳካት የሚንቀሳቀሱ፣ ቅንጣት ታክል ህዝብን የሚጠቅም ጥያቄ ስለሌላቸው በነፃ ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ የትግል** ***መድረክ ፈፅሞ ኣይመርጡም፡፡*** የህዝብን ሉኣላዊነት የተቀበለ፣ ለህዝብ የሚጠቅም ዓላማ ስላለኝ ህዝብን በማሳመን ዓላማየ ኣሳካለሁ ብሎ የሚያምን ብቻ ነው ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊ መንገድ የሚመርጥ፡፡

## 6.3 የትምክህትና ጠባብነት አንድነት

ጠባቦችና ትምክህተኞች አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ሁለቱም ፀረ ህዝብ በመሆናቸው ዓላማቸውን የሚሳካ በፀረ ህዝብ ተግባራትና በፀረ ዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ እንደ ሆነ ስለሚያምኑ የጥፋት መንገድ የሚመርጡ መሆናቸው ነው፡፡

እነዚህ ፀረ ህዝብ ሃይሎች፣ አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርና ስርዓታችን ህዝባዊ መሆኑ ያውቃሉ፣ ማወቅ ብቻ ሳይሆን ከልብ ያምናሉ፡፡ *ግን ደግሞ የነሱ ፍላጎት ስልጣን በመያዝ ከህዝቡ በላይ መጠቀም በመሆኑ፣ ይህም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መንገድ ማሳካት ስለማይቻል ይቋወሙታል /በውሸት መንገድ በመመራት/፡፡* አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን የሁሉም ዜጎች መብት በእኩል የሚያከብር በመሆኑ፣ ለሁሉም እኩል የመልማት ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ጠባቦችና ትምክህተኞችን ይህንን መብት ተገን በማድረግ ለአፍራሽ ተግባራት መጠቀሚያ እንደሚያደርጉት ምንም ጥርጥር የለውም፡፡

ለምሳሌ በጎንደር አንድ ኪራይ ሰብሳቢ ፀረ ህዝብ ያደረገው ነገር ስናይ **ፖሊሶች እጁን እንዲሰጥ ሲጠይቁት ሚስቱና ልጆቹ እንደ ምሽግ በመጠቀም የፖሊሶችን ሂይወት አጥፍቷል፡፡** የፀረ ህዝቦች ተግባር ሁሌም ህዝብ እንደ ምሽግ በማድረግ የህዝብ እልቂትን ማምጣት ነው፡፡ የኛዎቹ ትምክህተኞች ለየት የሚያደርገው ግን ከሰው ፍጡራን በተለየ ሁኔታ ሚስቱና ልጆቹ አሳልፎ መስጠቱ ነው፡፡ የወጣለት ፀረ ህዝብ ማለት ይህ ነው፡፡ ከዚህ ተግባር መገንዘብ የሚቻለው፡-

1. *ዴሞክራሲያዊ ልማታዊ መንግስታችን ለህዝብ የቆመ፣ ስለ ህዝብ ብሎ መስዋእት የከፈለ፣ አሁንም ስለ ህዝብ ብሎ መስዋእት የሚከፍል እንደሆነ፣ ስለህዝብ መስዋእትነት በመክፈል ላይ ያለ ሞሆኑ ህዝባችን ይገነዘባል፣* እነዚህ ፀረ ህዝቦችም ይህንን ጠንቅቀው ያውቃሉ፡፡ ምስክርነቱም ቤተሰቦቻቸው እንደ ምሽግ መጠቀም ማለት መንግስት ነፃና ኢኖሰንት ወገን ከመግደል መስዋእት መክፈል እንደሚመርጥ ስለተረዱ ነው፡፡
2. የዚህኛው ድራማ ሁለተኛው እንድምታ ፀረ ህዝቦች ሁሌም ዓላማቸው የግል ጥማትን ማሳካት በመሆኑ **መጀመሪያ ለመስዋእትነት የሚማግዱት ህዝቡን ነው፣ ከህዝብ በስተጀርባ ሆኖው ነው የሚያዋጉት፣ የተለመደው የነሻዕብያና የአሸባሪ ሃይሎች እንቅስቃሴ በምናይበት ጊዜ ህዝብ ማኽል ሆኖ ነው ጥይት የሚተኩሱት፣ የኛዎቹ ፀረ ህዝቦች ግን ለልጆቻቸውም መስዋእት የማይከፍሉ እልም ያሉ ፀረ ህዝቦች ናቸው፡፡** የነዚ ፀረ ህዝብነት ከልክ ያለፈ ነው፡፡ የፖሊስና የመከላከያ ሰራዊታችን ለህዝብ ሲሉ ግንባር ቀደም ወይም **የሰላ ጫፍ ሆኖው መስዋእት ሲከፍሉ፣ የኛ ጠባቦችና ትምክህተኞች ይቅር ለህዝብ መስዋእትነት ሊከፍሉ፣ ማንኛውም የእንስሳ ፍጡር የሚያደርገውን ለወለዱዋቸው የሚከፍሉትን መስዋእት ያክል ለቤተሰቦቻቸው**

የማይከላከሉ፣ እንዲያዉም አግተው እንደ ምሽግ በመጠቀም በስተጀርባ ሆኖው የጥፋት ተግባራቸው የሚፈፅሙ ወራዳ ሃይሎች ናቸው፡፡

ታድያ ለነዚህ ሃይሎች ምን እንዲያደርጉ ነው ዕድል የሚሰጣቸው? እዚህ ላይ ቆም ብሎ ማሰብ በጣም ያስፈልጋል፡፡ ለንደዚህ አይነት አደገኛ አስተሳሰብ ቦታ መስጠት ማለት ራስን ፀረ ህብነት መሰለፍ ማለት መሆኑ በደንብ መገንዘብ አለብን፡፡

## 7 የተረጋጋች የለማች ኢትዮጵያ የመፍጠር ጉዳይ ለመንግስት ብቻ የሚተው ጉዳይ አይደለም

እገራችን በዓለማችን ምርጥ ተሞክራ ያላት አለማችን በኤኮኖሚ ቀውስ ብምትናጥበት ጊዜ ለዓለም ያስደነቀ ፍትሃዊ ፈፃን ዕድገት በማስመዝገብ ላይ ያለች አገር፤ ***በትግራይ ተወላጆች ላይ ደበል ሲደርስ ዝምብሎ የሚያይ ካለ በጣም ተሳስቷል፣ ዛሬ በትግራይ ተወላጆች የደረሰውን ግፍ ነገ በአማራ፣ በኦሮሞ፣ በደቡቡም በሌሎችም ላይደርስ ምንም ዋስትና የለውም፡፡*** እነዚህ ሃይሎች ይቅርና ለህዝብ ሊቆሙ ልጆቻቸውና ሚስቶቻቸው ኣሳልፈው የሰጡ ሃይሎች ናቸው፣ ጨካኞች ናቸው፣ እነሱ እንዲደላቸው ህዝቡን ወደ እሳት የሚማግዱ፣ የተጀመሩትን የልማት ስራዎች የሚያቆሙ ብቻ ሳይሆኑ የሚያወድሙ አረመኔዎች ናቸው፡፡ ***ስለዚህ ለነዚ ወሮበሎች በግላጭ፣ በአደባባይ ማውገዝ ብቻ ሳይሆን ሕግ ፊት በማቅረብ መግጠም ነው ያለብን፡፡***

በርግጥ ነው በጣም ብዙ ያልተመለሱ የህዝብ ጥያቄዎች ኣሉ፣

- የመልካም ኣስተዳደር ጥያቄዎች ኣሉ፤
- የኪራይ ሰብሳቢነት ችግሮችን የመፍታት ጥያቄዎች ኣሉ፤
- የመሰረተ ልማትና አጠቃላይ የፈጣንና ፍትሃዊ ልማጥ ጥያቄዎች ኣሉ፤

***እነዚህ ጥያቄዎች መጠየቅ አለባቸው፣ መልስም ማግኘት አለባቸው፡፡ እነዚህ የህዝብ ጥያቄዎች መልስ የሚሰጥ ህዝባዊ ድርጅት ወይም ህዝባዊ ወገንተኝነት ያለው ስርዓት ብቻ ነው፡፡*** ስለዚ ፀረህዝቦች፣ የነመላኩ ተፈራ ቡችሎች፣ የፊውዳልና የደርግ ርዝራዦች፣ እንደ ኦነግ፣ ኢህአፓና ጉንበት 7 የመሳሰሉ የሻዕብያ ተላላኪዎች ይህንን የህዝብ ጥያቄ ተገን በማድረግ የጥፋት ተግበራቸውን ለመፈፀም በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ለሰዓታትም ለደቂቃዎችም ቢሆን ዕድል መስጠት የለበትም፡፡

***ዴሞክራሲያዊ አንድነታችንን የሚፈታተን አንድን ህዝብ ማዋረድ፣ ማንቋሸሽ፣ ሃብቱና ንብረቱን ማውደም፣ መዝረፍ፣ በማንነቱ እንዲሸማቀቅ ማድረግ፣ ይቅር ለወገን ለባዕድም መደረግ የሌለበት አስነዋሪ ተግባር ነው፡፡ ማንም በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ አንድነት የሚያምን ወገን ማውገዝ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ይህንን ዝም ብሎ ማየት ቤቱን እየተቃጠለ ዝምብሎ ማየት ማለት ነው፡፡***

የጎንደር ህዝብ በትግራይ ህዝብ ላይ የደርስ የነበረው የወረበሎች እንቅስቃሴ ዝም ብሎ አልተመለከተም፣ የትግራይ ተወላጆች ልጆቻቸው ከጥቃቱ ተከላክለዋል፣ ውድና አስፈላጊ ንብረቱ ደብቆ ከውድመትና ከዝርፊያ ለማዳን ሞክረዋል፣ ሊደርስ የነበረው አስከፊ ግድያና እልቂት ተከላክሎላቸዋል፣ ***የነዚ አረመኔ ወሮበሎች እንዳሰቡት እንዳይሆን የፌደራል ፖሊስና የፀረ ሽብር ሃይሎች ከጎንደር ህዝብ በጋራ ባይከላከላቸው ኖሮ ምን ይሆን እንደነበር ለማወቅ ኣያዳግትም፡፡*** እነዚህ ወሮበሎች ለሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው በምሽግነት የተጠቀሙ፣ የፌደራል መንግስትና የጎንደር ህዝብ ባይታገላቸው በትግራይ ተወላጆች ላይ ሊያደርሱት የሚችሉት ጥፋት በቀላሉ ሊገመት የማይችል ጠባሳ ያሳድሩ ነበር፡፡

በርግጥ እነዚህ ሃይሎች ያለ ውጭ እርዳታ ይህን ኣላደረጉም፣ ከውጭ ለጥፋት የሚያገለግል ገንዘብና መሳሪያ ስለተሰጣቸው እንደዚህ አይነት ውድመት ለማድረግ ዓቅም ፈጥሮላቸዋል፣ እንዲደራጁ እንዲጠናከሩ ዕድል ሰጥቷል፡፡ ***ግን ዋናው ነገር የውጩ ገንዘብና ድጋፍ ሳይሆን ከውስጥ ይህንን አፍራሽ ተግባር የመመከት አቅም በሚገባ ያለመገንባት ነው፡፡***

አሁን ያለንበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መጠበቅ ያለበት በጥቂት የድርጅት ኣባላት ሳይሆን በህዝቡ ነው፡፡ ህዝቡ የዚህን ስርዓት ተጠቃሚ እንደሆነ በተግባር መመስከር ኣለበት፡፡ በርግጥ ህዝቡ የዚህ ስርዓት ተጠቃሚ እንደሆነ መስክረዋል፡፡ ***ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችን ምልአተ ህዝቡ ወይም 100% እንኳ ባይባል በዴሞክራሲያዊ አሰራር መሰረት ተወዳድሮ ዋጋ ካለው 33,201,969 የኢትዮጵያዊ ድምፅ ውስጥ 27,347,332 ወይም 82.4% ድምፅ በማግኘት በሁሉም የተወዳደረባቸው የፌደራል ተወካዮች ምክርቤት ወንበሮች ሙሉ በሙሉ 100% አሸንፏል፡፡*** ይህም አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን በተወዳደረባቸው ቦታዎች ሁሉም በማሸነፍ ያለ ምንም ተቀናቃኝ መንግስትነት ተቆጣጥሮ በማስተዳደር ላይ ይገኛል፡፡

ይህ ሲባል ግን 82.4% መራጭ ምንም ችግር የለባቹሁም ብሎ ስርዓታችንን መረጠው ማለት ኣይደለም፡፡ ችግሮች አለባቹ ግን ደግሞ መፍታት የምትችሉትም ራሳቹ ናቹ በማለት ያሉንን

ችግሮች በሙሉ በመዘርዘር ነግሮን ነው የመረጠን፡፡ ***ይህ በእንዲህ እንዳለ 17.6% መራጭ ደግሞ ስርዓቱን በመቃወም ለሌላ መርጧል፡፡*** ይህ በፌደራል የተወካዮች ምርጫ ላይ ነው፡፡ በክልሎች የምርጫ ሁኔታ በምናይበት ጊዜ አጠቃላይ ውጤቱ ተመሳሳይ ሲሆን ግን ደግሞ በክልል ላይ ግን የተሻለ ድምፅ የተገኘ ሲሆን ከክልል ክልል ግን መጠነኛ ልዩነት አለው፡፡

ለምሳሌ የያንዳንዱ የኢህአዴግ ብሄራዊ ድርጅት የተወዳደረባቸው ክልሎች ውጤት ስናይ፡-

| ተቁ | ክልል | የኢህአዴግ ብ/ድርጅት | የመረጠው ህዝብ | የመረጠ በ% | ያልመረጠው ህዝብ | የልመረጠ በ% | ጠቅላላ መራጭ | የወንበር ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ትግራይ | ህወሓት | 2,374,574 | 99.39% | 14,574 | 0.61% | 2,389,148 | 152 |
| 2 | አማራ | ብአዴን | 7,314,564 | 96.92% | 232,448 | 3.08% | 7,547,012 | 294 |
| 3 | ኦሮሚያ | ኦህዴድ | 10,877,190 | 93.12% | 803,641 | 6.88% | 11,680,831 | 537 |
| 4 | ደ/ብ//ህ | ደኢህዴን | 5,836,849 | 93.74% | 389,787 | 6.26% | 6,226,636 | 345 |
| | ጠቅላላ | | 26,403,177 | 94.8% | 1,440,450 | 5.2% | 27,843,627 | |

በክልሎችም በተመሳሳይ መንገድ ከ93.12% እስከ 99.39% ህዝብ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት የመረጠ ቢሆንም እንከን የለሽ ብሎ ኣልመረጠም፣ በተጨማሪ ከ0.61% እስከ 6.88% የሚሆን መራጭ ስርዓቱን ከልብ ኣላመነበትም፡፡

ስለዚ ይህ ለክልል ተወካዮች ምክርቤት ከ0.61% እስከ 6.88% የሚሆን መራጭ እንዲሁም ለፌደራል ተወካዮች ምክርቤት እስከ 17.6% ያልመረጠን ህዝብ በስርዓታችን ላይ ጥርጣሬ ያሳደረበት ምክንያት በደንብ ተለይቶ ማወቅና መፍትሂ መደረግ ኣለበት፡፡

***አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓታችን ከጥቂት ክራይ ሰብሳቢ ግለሰቦችና የጥፋት ሃይሎች በስተቀር ምልኣተ ህዝቡን ተጠቃሚ የሚያደርግ ስርዓት እያለ ከመራጩ እስከ 17.6% ወይም ደግሞ በ5,854,637 ያህል ህዝብ ያለመመረጡ ኣሳሳቢ ነው፡፡*** ከዚህ በተጨማሪ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓታችን ህዝብን ተጠቃሚ በማድረግ ወደር የሌለው አማራጭ ቢሆንም፣ የመረጠንን 82.4% መራጭ ያስቀመጣቸውን የመልካም ኣስተዳደር ችግሮችን ቶሎ ካልተፈቱ፣ ህዝቡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓታችን ጥርጣሬ ማሳደሩ የማይቀርና ብሎም ለስርዓቱ ጠበቃ ከመሆን ይልቅ ለዘብተኝነት ሊያጠቃው ስለሚችል ጊዜ ሳይሰጡ ቶሎ የመፍታት ጉዳይ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ ኣለበት፡፡ ***ይህ ችግር ያለመፍታት ማለት በእጅ ያለ ወርቅ እንደሚባለው በስንት መስዋእትነት የተገኘው የህዝብ ድል በዋዛ ፈዛዛ በመልፈስፈስ ማባከንና አገራችን ወደማያባራ ችግር መዳረግ ማለት ነው፡፡***

# 8 ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በገዢዎቹ ይደርሰው ከነበረውን ምሕረት የለሽ ጭቆናና ሲቃይ ለመላቀቅ ለዘመናት በተደራጀና በተናጠል ሲያደርገው የነበረ ትግልና የከፈለው ከፍተኛ መስዋእትነት በድል መቋጫ ያገኘበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር አመራር የተደረገ ትግል ብቻ ነው፡፡

አገራችን ኢትዮጵያ፣ ከደርግ ውድቀት ማግስት 17 የታጠቁ ድርጅቶች አብዛኞቹ የነፃነት ጥያቄ በመያዝ የታገሉና እኩይ ዓላማቸው ለማሳካት ሴላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገዱም ፀረ ሰላምና የሽብር መንገዱም እየቀላቀሉ በሚታገሉበት ወቅት፣ በቃ አለቀላት የነዩጎዝላቭያና የሶማሊያ ዕጣፈንታ ይገጥማታል ተብሎ ሲነገርላት በነበረው ወቅትም ***<u>በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር አመራር ነበር አስቸጋሪው ወቅት በማለፍ ህገ-መንግስታዊና የተረጋጋ ስርዓት ለመገንባት የበቃነው፡፡</u>***

አገራችን በዓይነቱ ዴሞክራሲያዊና በሰፊው ህዝብ ተሳትፎ የተደረገበት ህገመንግስት ካፀደቀች በኋላ ምንም እንኳ ሰላምና መረጋጋት በማስፈን እንዲሁም በአማካይ 5 በመቶ ዕድገት ብታስመዘግብም፤ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ዘለቄታ ያለው ልማት ማስመዝገብ ተስኗት፣ ድርጅታችን ኢህአዴግ የመበስበስ አደጋ አጋጥሞት፣ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ እሴቶቻችን መሸርሸር ጀምሮው የፀረ ዴሞክራሲ አስተሳሰብና ተግባሮች ማቆጥቆጥ ሲጀምሩ፤ ***<u>አሁንም በአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመርና አመራር ነበር ወደ ተሃድሶ በመግባት አብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመራችን የልማታዊነትን ተልዕኮ በመጨመር የህዳሴ ጉዞን መጀመር ያበሰረን፡፡</u>***

ኢህአዴግ ከመበስበስ አደጋ ተላቆ አገራችን በተቻለ ፍጥነት ከድህነት ወጥታ በመካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ለማሰለፍ የረጅም ጊዜ ራዕይ አስቀምጣ እንዴት መድረስ እንዳለባት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ቀይሳ፣ ሊያጋጥሙ የሚችሉና እያጋጠሙ ያሉትን ችግሮች መንስኤዎቻቸውና መፍትሂዎቻቸው በግልፅ አስቀምጣ፣ መሆን ያለበት የትግል አቅጣጫ ለይታ፣ ይህን ተግባራዊ በማድረግ ***<u>አገራችን ኢትዮጵያ በልማት ጎዳና ከዓለማችን ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ልማት ከሚያስመዘግቡ አገራት ቀዳሚ ስፍራ የምትይዝ አገር፣ ያደረጋት ይህ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ወይም ደግሞ በአሁን አጠራር ልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግስት መስመር አመራር ነው፡፡</u>***

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም የልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስታችን የምልአተ ህዝቡ ጥቅም የሚያስከብር፣ በአገራችን ህዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ እኩልነታቸውን በማረጋገጥ ***ዴሞክራሲያዊ አንድነት በመገንባት ላይ ያለ፣ የግልም የቡድንም መብት በማረጋገጥ አኳያ ብቸኛ ርዕዮት የሆነ፣ በህዝባችን ልብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሰፊ ተቀባይነት እምነት በማግኘት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰ የህዝቡን ኑሮ በመቀየር ላይ ያለ መስመር ነው፡፡*** ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ መስመር ውጭ ያለ ሁሉ የውድቀት፣ የብተና፣ የግርግር በአጠቃላይ የኪራይ ሰብሳቢነት መንገድ ነው፡፡

ስለዚ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የአንድ ፓርቲ ወይም ደግሞ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የብሄር ብሄረ-ሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብት የማስከበርና ያለማስከበር ጉዳይ፣ ፈጣን፣ ፍትሃዊና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥና ያለመረጋገጥ ጉዳይ፣ ዴሞክራሲያዊ ኣንድነቷ ተከብሮ በፖለቲካም በኢኮኖሚም ተሰሚነት ያላት አንድ ጠንካራ አገር የመፍጠርና ያለመፍጠር ጉዳይ፣ በአጠቃላይ የአገራችን የህልውና ጉዳይ ነው፡፡ ***ስለዚህ አባቶቻችን ከባዕድ ወረራ ጠብቀው ያስረከቡን አገር እንደ አባቶቻችን ለቀጣይ ትውልድ ዳርድንበርዋ ብቻ በማስከበር ሳይሆን ከድህነት ወጥታ የበለፀገችና ዴሞክራሲያዊት አገር ለማስረከብ ሁላችን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጥላስር መሰባሰብ አለብን፡፡***

# አብዮታዊ ዴሞክራሲ ወይም ልማታዊ ዴሞክራሲ መንግስት ለኢትዮጵያ የአማራጭ ጉዳይ ሳይሆን የህልውና ጉዳይ ነው!!!

## ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ጎን በመሰለፍ የህዳሴ ጉዟችን እናስቀጥል

***ስላነበባችሁልኝ ከልብ አመሰግናለው፣ ደጋግማቹ ብታነቡልኝና አስተያየት ብትፅፉልኝ በበለጠ እደሰታለሁ፡፡ ቸር እንሰንብት***

## ከህዳሴ ኢትዮጵያ

## ሓምሌ 30፣ 2008 ዓ.ም.